ታሪካዊቷንና ብርቅ ድንቋን የቤተ ክርስቲያኗን በርና መስኮት ሰበሩባት። ዛሬ ምዕመናኑ ለሁለት አልተከፈሉምን? ያውም በሚያስቅና በሚያሰቅቅ መልኩ እንጂ! የኛ ሰው ናቸው መደገፍ አለብህ በሚለው መልኩ እንጂ! ይህ አባባል ሁለት ፊት አለው። አንዱ የፖለቲካ የድርጅታችን ሰዎች፤ ሁለተኛው የኛ አካባቢ የሚል ነው። ይህ አባባል ከአቡኑ ደጅ ይከትማልን? እንዴት ተደርጎ? ይህ አባባልና አስተሳሰብ ደግሞ አብሮ – አደግ እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል። በአደባባይም ይናገሩታል። ሲጀመር ጀምሮ «ሲወለድ ያጠለቀው ሲሞት አወለቀው።» ነው የሚሉ ብዙ ናቸው። ሁሉም አይደሉም። ግን ጥቂቶቹ አዎ ናቸው።

እኔ በግል የማውቃቸው አባት ወደ ምንኩስና ዓለም ከገቡበት ቀን ጀምሮ ከሥጋ ወላጆቻቸውና ከእኅት ከወንድሞቻቸው በአጠቃላይ ዘመዶቻቸው ተለያይተው እንደቀሩ ምስክር ነኝ። እንኳን የመንደሬ ሰው ነው ብለው ሊናገሩ ይቅርና የመነኩሴ አገሩ በዓቱ የዋለበቱና ያደረበቱ የሚሉ ናቸው። አጋጣሚ ሆነና ለኔና ለኞ እንደሚሉት ከሌላው ጋር ገጠማቸው ስደቱ አገናኛቸው። ሌላው አባት ግን አቡን ዘበስማያት ከመድገም ይልቅ የት ተወለድህን? ከየት መጣህንን? አሥራ ሁለት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ዓርባ ዘጠኝ ጊዜ ሲሉና ሲታከቱ የሚያድሩ ከመሃላቸው እንዳሉ ሁሉም ይመሰክርላቸዋል። እንደ መልካም ተግባር ተቆጥሮ የሚያሸልም ቢሆን ምንም ዓይነት ተወዳዳሪ የላቸውም። የሚያሳዝነው ግን እንደኔ አመለካከት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አሜሪካ ገብቼ ሥልጣኔን አደሼ ይህችን ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ከፍዬ ኤጲስ ቆጶሳትን ሾሜ ትርምሱን አወጣዋለሁ ብለው የሚመኙና የሚያስቡ አባት አልነበሩም። ነገር ግን ኀበ ወሰድዎ በመሆናቸው ከመጀመሪያዋ ቀን እስከ መጨረሻዋ ቀን ድረስ እንኩ ያድርጉት ተብሎ በተሠጣቸው በትረ ክህነት ፈቃደ ሰብእ ፈፃሚ ሆነው የነበሩ ያሉና የሚኖሩ በመሆናቸው እንጂ ቢያንስ ቢያንስ ይህን እንመሰክርላቸዋለን።

አሁን ጉዳዩን መለስ ብለው ሲያዩትና ሲመለከቱት የሚያዝኑበት ይመስለኛል። አዎ የሚታዘንበት ነው። ኃሳባቸው ትክክለኛ ነው እውነት ነው ብለው የሚቀርቧቸው ሰዎች የሚያሳይዋቸው መንገድ የማይዘልቅ ዳር የማያስወጣ ነው። በዚህ ዓይነቱ ጎዳና ጉዞ መጀመሩ ደግሞ እንደኛ የአካባቢው እንግዳ መሆንን ያመለክታል። ሁለተኛ ጊዜንና ያለ የሌለውን ኃይል ካልሆነ መንገድ ላይ በከንቱ መጨረስ ነው። አሁን ሲያደርጉ የሚታየው ካንዳንድ ከተሞች ከአውሮፕላን ወርደው ወደ ሠፈር ሲሄዱ ምዕመናን የሚከራዩላቸው ሊሙዚን በመዝሙርና በሞተር ሳይክል



ሲያጅቧቸው በዚያ ሁኔታ ኢትዮጵያ የሚሄዱ ይመስላል። ነገር ግን ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ የሚያስሄድ መኪና መንገድ እኮ የለም። ያለው ብቸኛ መጓጓዣ አውሮፕላን ነው። በአውሮፕላን ግን ኢትዮጵያ ሄደው መኖር ይችላሉ። ተቀባይም ወንድሞቻቸው አሉ። ጥሪውም ውትወታውም እሱው ነው። እንዲህ የሁሉም ልብ በኃዘን ከሚናወጥና ከሚታወክ ቢሄዱ ለእነሱም ፍቅር ለቤተ ክርስቲያናችንም ክብር ነው።

ዛሬ አሜሪካ ያለው ኑሮ ጣዕሙን እያጣ እየገረጣና እንደ ኗሪዎቹ እየነጣ ነው። ሲሆን ወደ አገራችሁ ተመለሱ። የግብርና ሙያ ያላቸውን ሂዱና መሬት ቆፍሩ እረሱ ምሁራኑን የአገራችሁን ማዕድን አስሱ ሁላችሁም በፍቅር ተመላለሱ። ካህናቱም አገራችሁን አወድሱ ብላችሁ ብትመክሩ የሁሉንም ጆሮ በመስቀላችሁ ትዳስሱ። በስደት ከሠላሳ ዓመት በላይ መቆየት ያገር ጉዳት ለየራሱም ታላቅ ናፍቆት ነው። ከዚህ መሆን ትርፉ እጅግ መዋተት ነው። መማር መመራመር መልካም ነገር ለመፍጠር ነው። ስለዚህ እናንተም ግቡ ሌላውንም አስገቡ። ኢትዮጵያን የፍቅር የሰላም አውድማ ትሁን። ይህን ማድረጉ የአባትነት ግዴታችሁ ይሆናል። ያለበለዚያ ግን ከጠላት ጥፋት የምትጠብቋትን ቤተ ክርስቲያናችሁን ጥላችሁ ወጥታችሁ ምዕመናን የራሳቸውን ቤት በውጭ ዘግተው እንዲያቃጥሉ እሳት ማቀበል ነው።

ይሁንና ይሁን እንጂ! ዞሮ ዞሮ ተኀጅዎች በቅድሚያ እናንተው ከዚያም የቤተ ክርስቲያናችን ታሪኳ ማንነቷና በጠላቶቿ ዘንድ መሳለቂያ መሆኗ ነው። ከዚህ ዓይነቱ ፃማ ወድካም እንድንወጣ እርዱን። ይህን የመሰለውን በጎ ነገር ለመሥራት ምከሩን። አርዓያም ሁኑን። «ለዘኀለፈ ሥርየት ወለዘይመጽእ ዕቅበት» [ላለፈው ይቅርታ ከሚመጣው ጥበቃ] የሚሆነው ከዚህ ላይ ነው። አሁን ወደ ጣራው የምትወጡበት መሰላል በቅርቡ ይሠበራል። ከዚያ በኋላ ከወረዱ መውጣት ከወጡ መውረድ መመላለስ ያበቃል። ያም ፍፃሜ ዘመን ይሆናል። ምሳሌው የዓይነ ሥውሩ መሸፈት ይሆናል። አንድ ዓይነ ሥውር የሕዝቡን ልብ ለመስቀል ሸፈተ ተብሎ እንዲነገርለት ከጓሮው ከሚገኝ ጎመንዘር ውስጥ ይደበቃል። ሁለት ቀን ያለምንም ኮሽታ ይውላል ያድራል። በሦስተኛው ቀን ባጠገቡ የሚያልፍ የሰው ዳና ይሰማና አንተ ስለኔ ምን ይወራል? ሕዝቡስ ምን ይላል? ሲል ይጠይቃል። ተጠያቂም ያው ጥጋበኛ እውር ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ ወድቆ ይሆናል ይባላል ይለዋል። እውነቱ እንደዚያ ነውና ነው። እሱ ግን የጠበቀው ሸፍቷል አገር ተጨንቋል ታውኳል እንዲባልለት ነበር። ይህንን ምሳሌ አባቶች

ቅዱስ እስጢፋኖስ ነው። ዝርዝር ታሪኩን ለመከታተል የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሦስት ከቁጥር ሦስት እስከ ስድስት ድረስ ያለውን ያንቧል።

የዲቁና ክህነት ቀደም ባሉት ዘመናት በተለይም ክህነት መሠጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ጊዜ ድረስ ክህነቱን የሚቀበሉት ዲያቆናት በሕግ የተወሠኑ ማለት ሚስቶች ያሏቸውና ተገቢውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስጫ ትምህርት በበቂ ተምረው ያጠናቀቁ ምሁራን ነበሩ። ከዲቁናም በቀጥታ ወደ ቅስና ይሸጋገሩ ነበር። ነገር ግን ከግራኝ አህመድ ወረራ በኋላ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ። አገልግሎታቸውም ተቋረጠ። ስደትም ሆነ። ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወርና መሸሽግም ሆነ። በዚህ ሁናቴ አሥራ አምስት ዓመታት ብዙ መጉላላት በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ሆነ። ብዙ ካህናትም በጦርነቱ አለቁ። ከግራኝ አህመድ ወረራ በኋላ የተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት መቃኞ እየሠሩ መቀደስ ሲጀምሩ አገልግሎት የሚሠጡት በሕግ የተወሠኑ ዲያቆናት ቁጥር ቀነሰ። ስለዚህም አገልግሎቱ መታጎል ጀመረ። ለዚሁም መፍትሔ ሆኖ የቀረበው ገና በትምህርት ላይ ያሉ ወጣት ልጆችን የዲቁና ክህነት እየሰጡ ማስገልገል ተጀመረ። በዚህም ምክንያት እንደ ልማድ ተቆጥሮ ገና ሕግ ለመሥራት ያልደረሱትን ልጆች ክህነት መስጠት ቀጥሎ እስካሁን ድረስ አለ። ይሁንና ለአቅመ አዳም ሲደርሱና ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ሕግ ሠርተው በሥጋ ወደሙ ተወስነው ከዲቁና ወደ ቅስና እንዲሸጋገሩ ሆኗል። ስለዚህ ከዲቁና ወደ ቅስና በሕግ ተወስኖ ማለት ሚስት አግብቶ ወይንም በምንኩስና ተወስኖ ወደ ቅስና መሸጋገር ናቸው። ስለዚህ የቅስና ሥልጣነ ክህነት የሚገኘው በሁለቱ መንገዶች በኩል ብቻ ነው።

## ቅስና

ቅስና ከፍተኛ የሥልጣነ ክህነት ማዕርግ ነው። ሥልጣኑም የሚገኘው ወይንም የሚሾሙት በኤጲስ ቆጶስ ብቻ ነው። ይህ ሥልጣነ ክህነት ሥጋ ወደሙን ወደ ኢየሱስ ሥጋ ደሙን ወደ ኢየሱስ ደም ይለውጣል። ያጠምቃል መንፈስ ቅዱስን ያሰጣል ይቀድሳል ያቆርባል ይባርካል ይናዝዛል ኃጢዓት ያስተሠርያል። ይገዝታል ይፈታል ያነጻል ይቀድሳል። ይጸልያል ኃጢዓት ያስተሠርያል። አሁንም የዚህ ሥልጣነ ክህነት ምንጩ ወይንም መገኛው ከኤጲስ ቆጶሱ ነው። ከቅስና ያለው ሥልጣነ ክህነት የውስጥ አገልግሎት መስጫ እንጂ የሹመት ስም አይደለም። ቅስና ግን



ሹመትም መጠሪያም ነው። ስለዚህም ቀሲስ ወይንም ቄስ እገሌ እየተባለም ይጠራል።

## ቁምስና

ይህ ሢመት የሚሠጠው ለመነኮሳት ብቻ ነው። ይህም ማለት ምንኩስና በሁለት መንገዶች የሚያዝ ማዕርግ ነው። አንደኛው በድንግልና የመነኮሰና ቅስና ያገኘ ሆኖ ለሁለተኛ ማዕርግ ቆሞስ ይሆናል። ሁለተኛው ደግሞ ሕጋዊው ካህን የሕግ ሚስቱ በሞት ስትለይ ወይንም ከካህኑ ጋር በሆነ ምክንያት አብራ ለመኖር ሳትችል ስትቀርና እሷን ትቶ በምንኩስና ለመኖር ሲፈልግ መመንኮስ ይችላል። በዚህን ጊዜ የቆሞስነት ሥልጣን ይሰጠዋል። ስለዚህ ሕጋዊው ካህንና ድንግላዊው መነኮስ ከቅስና በኋላ ሁለቱም ይቀበሉታል። ይሁንና ይህ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ካህናት ቆሞሳት ተብለው ይታወቃሉ። የሚሠጡትም አገልግሎት ሁለቱም በእኩልነት ቆብ ይባርካሉ ያመነኩሳሉ። አዲስ ቤተ ክርስቲያን ባርከው ታቦት ያስገባሉ። ይሁን እንጂ እንደ ምንኩስና ስም አባ ወይንም እንደ ቅስና ስም ቀሲስ ተብሎ እንደሚጠራ ቆሞስ አባ እገሌ ተብለው እንደ ሹመት ስም አይጠሩበትም። የተግባር ሹመት እንጂ የመጠሪያ ስም አይደለም። ይሁንና በከተማ ያሉ መነኮሳት የመጠሪያ ማዕርጋቸውን ከፍ ለማድረግ ሲሉ ቆሞስ አባ እገሌ ተብለው ሲጠሩ እንሰማለን። ትክክል አይደለም። ሹመት አሳሽ መሆን ነው እንጂ በብዛት ሥል ጣኑ ያላቸው እንኳን የሹመት ስም ሊያደርጉት ቀርቶ ቁምስና አላቸው ተብለው እንኳ እንዲነገር አይሹም።

ስለሆነም ሕጋዊው ካህን መንኩሶ ቁምስና ሲቀበል ለዚያ ካህን ይህ የሥልጣነ ክህነቱ ጣራ መሆኑ ነው። ይህም ማለት የመጨረሻው ማዕርግ ነው። ከዚህ በኋላ የሚቀጥለውን ሹመት የሚያገኙት ደናግላን እንጂ መአስባን አይደሉም። ይህንም የቤተ ክርስቲያኒቱ ቀኖና ደንግጎታል። ከዚህ ላይ ግን የደብር አለቅነትና የገዳም መምህርነት ሁለቱም ይሾማሉ ያገለግላሉ። ደናግላን መነኮሳት ከቁምስና ማዕርግ በኋላ የሚቀጥለው ማዕርግ ኤጲስ ቆጶስነት ነው።

## ኤጲስ ቆጶስነት

ከኤጲስ ቆጶስነት ማዕርግ ለመድረስና ይህን ከፍተኛውን ሢመት ለማግኘት በሙያ ማለት በትምህርት የበለፀገና ያወቀ በሥነ ምግባሩም የተመሠገነ ቀጥሎም በሚሠጠው አገልግሎት የተዋጣለትና ንቁ ለቤተ ክርስቲያኑ አገልጋይ የሆነ በምዕመናን ዘንድም እጅግ

የተሞገሠ አባት መሆኑ ሲረጋገጥና ሲታወቅ ለኤጲስ ቆጶስነት ምርጫ ይታጫል። ስሚመቱም ይወዳደራል። በምርጫ ካሸነፈ የመጨረሻውን የሥልጣነ ክህነት ማዕርግ ያገኛል። ከዚያም ስሙም ይለወጥና የኤጲስ ቆጶስነት ስም ይሠጠዋል በዚያም ይታወቃል። ይጠራልም። በሚሾምበት ሀገረ ስብከትም ስሙ ይጠራል ይጸለይለታል። ይህን ሹመት የሚሠጠው ቅዱስ ፓትርያርኩ ነው። ከዚህ በኋላ ያሉት ሹመቶች የማዕርግ እንጂ የሥልጣነ ክህነት ማዕርግ አይደሉም። በኤጲስ ቆጶሱና በፓትርያርኩ መካከል በሥልጣነ ክህነት አኩል ናቸው። በማዕርግ ግን ይለያያሉ። ከኤጲስ ቆጶስነት ማዕርግ በኋላ ጳጳስ ሊቀ ጳጳስና ፓትርያርክ የማዕርግ ሹመቶች ናቸው። ኤጲስ ቆጶሳት በአንድነት ፓትርያርኩን ይሾማሉ። ፓትርያርኩ ደግሞ ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾማል። አንድ ኤጲስ ቆጶስ ሲሾም ከሀገረ ስብከት ጋር ነው። ከተሾመበት ሀገረ ስብከትም እስከ ፍፃሜ ዘመኑ ድረስ ከዚያ ቦታ አይነሣም። በዕድገት በሊቀ ጳጳስነት ወይንም በፓትርያርክነት ከሆነ ግን ለከፍተኛው ማዕርግ ሥራ ይዛወራል እንጂ የተሠጠውን ሀገረ ስብከት ትቶ ወደሌላው አይሄድም በሌላው ሀገረ ስብከትም ሄዶ አይሾምም። ይህ ሥርዓት ግን ቅዱስ ሲኖዶሱ ያሻሻለው ይመስላል። ሊቃነ ጳጳሳቱን ካንዱ ሀገረ ስብከት ወደሌላው ሲያዘዋውራቸው ይታያል።

## ፓትርያርክነት

የጳጳሳቱ የሥልጣን ደረጃ እንዲህ ነው። ኤጲስ ቆጶስ የመጀመሪያው ሹመት ነው። ቀጥሎ ጳጳስ ይሆንና ሠፋ ያለ ሀገረ ስብከት ይሰጠዋል። ከዚያም ሊቀ ጳጳስ ሲሆን ደግሞ በሥሩ ኤጲስ ቆጶሳትን ሲመራና ሲያስተዳድር ነው። አሁን ግን ይህ ተሠርዞ ሁሉም ተጠሪነታቸው ለቅዱስ ሲኖዶስና ለቅዱስ ፓትርያርኩ ሆኗል። ከዚህ በኋላ ፓትርያርክ ለመሾም ሲፈለግ ከመካከላቸው ከአምስት ያላነሱ ከአሥር ያልበለጡ ተወዳዳሪዎች ቀርበው ከመካከላቸው አንዱ የድምፅ ብልጫ ያገኘው ብቻ ፓትርያርክ ሆኖ ይሾማል። ፓትርያርኩም የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ሆኖ ያገለግላል። ሊቃነ ጳጳሳቱን በቅርብ ይቆጣጠራል ሀገረ ስብከታቸውንም እየተዘዋወረ ይጎበኛል። የሥራም መመሪያም ይሠጣል። ሹመቱም የእድሜ ልክ ነው። ነገር ግን በሦስት ምክያቶች ብቻ ይተካል ወይንም ከሥልጣኑ ይለቃል። እኒህም ምክንያቶች ምንም እንኳ ቀደም ሲል የተገለጹ ቢሆንም ቅሉ ለአጽንኦተ ነገር ማለት ግንዛቤውን ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ ልድገማቸው። እነሱም አንደኛ በሞት ሲለይ፤ ሁለተኛ በገዛ ፈቃዱ ወዶና ተስማምቶ በገጠመው ችግር ሥልጣኑን ሲለቅና ሦስተኛ በእምነቱ ሕፀፅ ነውር



ተግባር ሲፈጽም ሲገኝ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ሥልጣኑን ይነጠቃል ይወገዛል። ካለ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ግን ምንም አይደረግም አይሆንምም። ስለሆነም የቅዱስ ሲኖዶሱ ውሳኔ ሁልጊዜም የበላይ ሥልጣን ያለው የጋራ ጉባዔ ነው። ከዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ውጭ የሚፈፀም ተግባር ሁሉ ቀኖና አፍራሽና የተወገዘ ነው። ስለዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ከአፎቱ የወጣ ሠይፍ ነው። ጳጳሳቱ በአንድነት የሚመክሩበት ጉባዔያቸውም ነው። እሱም በአጠራሩም ቅዱስ ሲኖዶስ ይባላል። ቀጥሎ እንመለከተዋለን።

## ቅዱስ ሲኖዶስ

ቅዱስ ሲኖዶስ ምንድን ነው? ቅዱስ ሲኖዶስ ከፍተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዋና የቀኖና የውሳኔ ጉባዔ ነው። ቅዱስ ሲኖዶሱ በፓትርያርኩ ሊቀመንበርነት ይመራል። ይህ የሊቃነ ጳጳሳት ጉባዔ ታላቅ ሥልጣን አለው። ይሾማል ይሽራል ያወግዛል ይፈታል የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት ይተክላል ይነቅላል ማለት ያሻሽላል አዲስ ሕግም ያወጣል። ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እየተባለ የሚጠራው የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግ የሚወሠነው በቅዱስ ሲኖዶስ ነው። የሚያሻሽለውም የሚሽረውም ይኸው ቅዱስ ሲኖዶስ ነው። የቅዱስ ሲኖዶስ ቃል ሠይፍ ነው ይቆር ጣልቃሉ ይሠራል። ቅዱስ ሲኖዶስም አንድ ብቻ ነው። በየሀገረ ስብከቱ ወይንም ጳጳሳቱ በሚሄዱበትና በሚቀመጡበት ይዘውት የሚንቀሳቀሱት የአገልግል ስንቅ አይደለም። የሚኖረውም ያለውም ከመንበረ ፓትርያርኩ ርእሰ ከተማ ብቻ ነው።

ቅዱስ ሲኖዶስ የሚሾምና የሚሽርም ነው። ከቅዱስ ሲኖዶስ ውጭ የሚሾምም የሚሽርም የለም። ቅዱስ ሲኖዶስ መክሮና መርጦ በሾመው ኤጲስ ቆጶስ ጳጳስ ወይንም ሊቀ ጳጳስ ላይ ጥፋት ከተገኘበት በቀጥታ የመሻር ሥልጣን አለው። ከቅዱስ ሲኖዶስ ውጭ የሚካሄደው ተግባር ሁሉ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ ነው። አንድ ጳጳስ ሥልጣነ ክህነቱ በቅዱስ ሲኖዶስ ከተያዘና ከተወገዘ ከሥልጣኑ ተለየ ነው። ክህነት አይሠጥም ቀድሶ አይባርክም የሥልጣን ዕጅ እግሩን አጣ ማለት ነው። በግዝት ላይ ያለ ጳጳስ መቀደስና ክህነት መሥጠት አይችልም። ነገር ግን ይህን ሲያደርግ ቢገኝ ማለት በታገደና ባልታደሰ የመንጃ ፈቃድ መንዳት ማለት ነው።

ቅዱስ ሲኖዶስ አንድና ብቸኛ ነው። አይቀዳም አይገለበጥም አይሰረቅም ከቦታ ቦታ አይዘዋወርም። ቅርንጫፍ መ/ቤትም የለውም። ለዚሁም በዓመት ሁለት ጊዜ በመላ አባላቱ ያሉበት የጋራ ጉባዔ ያደርጋል። በእነዚህ በዓመት በሚያደርጋቸው ሁለት ጉባዔዎች ሕግ ያወጣል ይወስናል የአስተዳደር መሸሻል ያደርጋል። በሲኖዶሱ ጽሓፊ አማካይነት የተለያዩ የመነጋገሪያ አርእስተ ጉዳዮች ይቀርባሉ። በእነዚያ ጉዳዮች ላይ በጋራ መክሮና ተወያይቶ ውሣኔ ያሳልፋል። ያ ውሣኔ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ይሠየማል በተግባር ላይም ይውላል። ለምሳሌ ያህል ቅዱስ ሲኖዶሱ ሊወሥንበት የሚገባው ጉዳይ እጅግም አጠያያቂ የሆነው ጉዳይ እስካሁንም ያልተፈታው ጥያቄ ሴቶች እናቶቻችንና እኅቶቻችን ካንዳንድ ገዳማት እንዳይገቡ ግዝት አለ። ይህን ግዝት አንሥቶ ሴቶችን በማንኛውም ጊዜና ሰዓትና ቦታ ሁሉ ገብተው እንዲጸልዩ መፍቀድ ይችላል። ይህን ውሳኔ የቀደሙ አባቶች ሲወስኑ የተለየና ከጊዜው ጋር የሚሄድ ችግር ኖሮ ይሆናል ከእነዚህ ገዳማት ሴቶች እንዳይገቡ ብለው የወሰኑት። በአሁኑ ጊዜ ግን በዓለም ላይ እንዲህ እንደኛው ብቻውን የቀረ ገደብ ጨርሶ የለም። ለምሳሌ ኢየሩሳሌም ጎልጎታ ላይ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ውስጥ ሴቶችም ወንዶችም ገብተው ይጸልያሉ። ይህን እንደምሳሌ ብንወስድ ይህን ችግር ቅዱስ ሲኖዶስ ተወያይቶ ግዝቱን አንሥቶ ውሳኔ ማድረግ ይችላል። ይህን የመሰለውን ጉዳይ ማንሣት የሚችለው ቅዱስ ሲኖዶሱ ነው። በዚህ አጋጣሚም ለቅዱስ ሲኖዶሱ ማመልከቻዬን አቀርባለሁ። ሌሎቹ እኅቶች ክርስቲያናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን የፆታ አድልዎ ጨርሰው አጥፍተውት ይታያሉ። በኛ ዘንድ ግን እንዲያውም እንደ ችግርም ቀርቦም አያውቅ። መነኮሳያቱም ለምን እንከለከላለን? ይፈቀድልን ብለውም አያውቁ። የተማሩትም እኅቶቻችን ይህ ግዝት ይነሣ ብለውም አያውቁም። እንደተከለከሉና እንደተባረሩ ቀርተዋል። ይህ ግዝት ወይንም ገደብ ቢነሣ እጅግ መልካም ይሆናል።

እናቶቻችንና እኅቶቻችን በየገዳማቱ ይኖራሉ አገልግሎትም ይሠጣሉ። የሴት ገዳምና የወንድ ገዳም ያሏቸው ገዳማት በብዛት አሉ። ታዲያ ካንዱ ገዳም ሁለቱንም ሲያስተናግድ ሌሎቹ ደግሞ የሴቶች እግር ገዳማችንን አይረግጠውም ለምን ይባላል? ጉዳዩ ወደ ቅዱስ ሲኖዶሱ የሚያቀርበውና እንዲወያዩበት ቢደረግ ይህን ገደብ ለማንሣት ችግር ያለበት አይመስልም። ጣና ደሴት ውስጥ ከሚገኘው ክብራን ገብርኤል ገዳም ሁላችንም ሴቶችም ወንዶችም ከጀልባ ስንወርድ ሴቶች በሙሉ ከአጥሩ ውጭ ከዚህ ቆዩ ተብለው ሲያዝኑና ይህ ነገር ትክክል ነው? ብለን ከእነሱ ጋር ስንወያይ ቆይተን ተለይተናቸው እኛ ወንዶቹ ልንጎበኝና ልንሳለም ወደ ቤተ



ክርስቲያኑ አመራን። እነሱ ቀሩ። ይህን ጥያቄ ከዚያ ለሚያስጎበኙን አባት ጥያቄውን አነሰሁባቸው። እንዲያውም እኛ በዘመኑ ለነበሩት ሊቀ ጳጳስ ለምን ውግዘቱን አታነሡትም ብንላቸው የአበው ድንጋጌ ስለሆነ እንዲያውም መጠናከር ይገበዋል ነው ያሉን ሲሉ አስረዱን። ገዳማቱ እንኳ ግዝቱ ቢነሣ ተቃውሞ የላቸውም። ሆኖም ውሳኔውን እነሱም እንደሚያስፈልግ ያምኑበታል። ታዲያ ቅዱስ ሲኖዶስ ወደፊት ሴቶች የክህነት አገልግሎት እንድንሠጥ ሹመቱ ይሠጠን ተብለው ሲጠየቁ መልሱ ምን ሊሆን ነው? ቢታሰብበት መልካም ነው። ስለሆነም ይህን የመሳሰሉትን ጉዳዮች ሊያሻሽል የሚችለው ቅዱስ ሲኖዶስ መሆኑን ለማመልከት ነው። ታዲያ እሁን የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔን በምንጠብቅበት ሁናቴ ላይ እያለን ራሱ ቅዱስ ሲኖዶሱ ችግር ላይ ነው ያለው። በማዕበል እንደሚንገላታ መርከብ ከወዲያ ወዲህ ይላል። የራሱ አባላት ሁለትም ሦስትም ሆናችሁ ብትሰበሰቡ ከመካከላችሁ እገኛለሁ የሚለው ቃል ለሲኖዶስ ተሠጥቶ ጳጳሳት በዋሉበት የሚውል ባደሩበት የሚያድር ኅቡዕ መንፈስ ሆኖ ይታያል። ነገር ግን ቅዱስ ሲኖዶስ የሁሉም የሊቃነ ጳጳሳቱ ሁሉ የጋራ ጉባዔ እንጂ እንደ ዳቦ እየተሸረፈ በኪስ ወይንም ባገልግል ተይዞ የሚዞር የመንገድ ስንቅ አይደለም። ይህ በዘመናችን እየተደረገ በማየታችን ያውም በበቁ በነቁ ዓለምን በናቁ አባቶች ዘንድ ይህ ትክክል ያለመሆኑን ኅሊናቸው እየተረዳው በዚህ ዓይነት ውጥንቅጥ ውስጥ መገኘቱ እጅግ የሚሰቀጥጥ ነው። ስለሆነም ቅዱስ ሲኖዶስ ሥልጣንና ተግባር ይህን ይመስላል።

# ፪ . ካህናት ዘበምድር

ና

ካህን የሚለው ቃል በጥሬ ትርጉሙ አገልጋይ ማለት ነው። የክህነት አገልግሎት ለማን? ለእግዚአብሔር ቤትና ለክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ አገልግሎት ሠጭነትና አቅራቢነት በአንብሮተ ዕድ [ዕጅን በመጫን] የተሠየመ ልዩ ምርጥ ሰው ማለት ነው። ለዚህም የአገልግሎቱ መሰጫ ተቋምም ቤተ ክህነት ናት። ፲ሚዎችም ሊቃነ ጳጳሳት ናቸው። የሥልጣነ ክህነት ባለቤቶች ጳጳሳት ብቻ ናቸው። አንድ ሕዝባዊ አባባል አለ ይህንኑ የሚያረጋግጥ እንዲህ ይላል። «ጳጳሱ ቄስ ናቸው ወይ? ቢለው ተርፏቸው ያበድራሉ» አለው ይባላል። ጥሩ ማስረጃ ነው። ስለዚህ ካህናት በቀጥታ የጳጳሳት ተበዳሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ተ፲ሚዎችም ናቸው። ዲቁና፥ ቅስና፥ ቁምስና የሚገኙት ወይንም የሚሠጡት አሁንም በጳጳሳት ብቻ ነው። ጳጳሳትን ደግሞ የሚሾማቸው ፓትርያርኩ ወይንም ሊቃነ ጳጳሳቱ በአንድነት ሆነው ነው። ይህ የፕትርክና ሥልጣን ደግሞ ለአንድ አባት ብቻ የሚሠጥ ሹመት ነው። መንበሩም አንድ ነው። ባንድ ወቅት ሁለት ፓትርያርኮች ሊኖሩ አይችሉም። መንበሩም ኢትዮጵያ ፓትርያርኩም አንድ የሚኖረውም መንበሩ ካለበት ቦታ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ብቻ ነው። ከዚያ ውጭ የለም። አይኖርም አይሆንምም። ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የሚፈቅደውና የሚያዝዘው ይኸው ነው። ከዚህ ውጭ ግን ሕጋዊ አይደለም። ይህን የሚቃወሙ የማይቀበሉ ግን የክህነት ሰዎች አይደሉም። ሥልጣናቸውም አይፈቅድላቸውም። አንድ መንበር ላንድ አባት እንጂ ለሁለት አይሆንም። ይህን ወደ ቀላል ምሳሌ ብንገልጸው አንዲት ሴት ሁለት ባሎች ልታገባ አትችልም። ይህንንም ክርስቲያናዊው ቀኖና ቤተ ክርስቲያን አይፈቅድም። ለዚህም ይመስላል ከውጭ ሲኖዶስ ከፍተናል የሚሉት አባቶች ሕጋዊ የሚል ቃል የጨመሩበት። የቃሉ መደመር ሕጋዊ አያደርገውም። ሁለት ጊዜ ዜሮ መልሱ ዜሮ ነው።

ስለዚህ ካህናት የሥልጣነ ክህነታቸው ምንጭ የሆነችዋን ቤተ ክርስቲያናቸውን ቀኖና መጠበቅ ማስጠበቅ የግድ ይሆንባቸዋል። ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካ በቡድን በምቀኝነት በማን አለብኝነት ስትከፋፈል ዝም ማለት አይሆንምም አይገባቸውም። ከራሳቸው ሕይወት ይልቅ ለቤተ ክርስቲያኗ ሕይወት የበለጠ ማሰብና መኖር



መቆጨት ከዚያም አልፎ ተርፎ መሞት ይጠበቅባቸዋል። የቤተክርስቲያኗ ሕይወት ካልኖረና አንድነቷ ካልተጠበቀ የእነሱ ሕይወት ዘለቄታ አይኖረውም። ከአካሉ የተለየ ራስ ብቻውን አይኖርም። እንደ ዮሐንስ ራስ በታምር ካልሆነ በስተቀር። ካህናቱ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ አገልጋዮች የሚሞሁበት የሚያስሞሁበት ጊዜና ወቅት አሁን ነው። ታሪክ የምትሠሩበት አሁን ነው። ያለበለዚያ ከቅርብ የምትመልሱትን ጉዳይ ርቆ ከሄደ ከሰው አዝመራ ከገባና ከተያዘ በኋላ ለመመለስ ሳይሆን የአፈላማ ከፍሎና አቤት ብሎ ማግኘት ነው። ከዚያ ይልቅ ዛሬውኑ መሮጥ መሽቀዳደም መጠበቅና መንከባከብ መሆንና መደረግ አለበት። ይህች ጊዜ ካለፈች በኋላ የሚሆነው ሙሽራው ከገባና በሩ ከተዘጋ እንደ ደረሱት አምስቱ ሰነፎች ቆነጃጅት መምሰል ነው።

በእርግጥ እውነተኞች ያልሆኑ በበሩ የማይገቡና ያልገቡ ምንደኞች ካህናት የሉም ማለት አይደለም አሉ። እንዲያውም ጊዜውንና ውዥንብሩን በትንፋሻቸው የሚያሟሙቁት እነሱ ናቸው። ከላይ እንደገለጽነው በካባው በቀሚሱና በመስቀሉ ለባሽነትና ተሸካሚነት እንጂ ጨርሶ ከሙያውም ሆነ ከሥልጣነ ክህነቱ የሌሉበቱ መች ለአሜሪካ ነፍስ እኔ አነስኳት ባዮች አሉ። ሁላችሁም እንደምታውቁት ባለቤቱ የሠነፈበቱ እንስሳ ያገኘው ሁሉ የሚጭነውና የሚገለገልበት አይደለምን? እንኳን ሃይማኖትን ከማንነት ጋር አጣምራ የያዘች ቤተ ክርስቲያን አስኬማ በለበሱ ዓለምን በናቁ ለነፍሳቸው ባደሩ እነ አባ ዓለም ለምኔ ከተሆነ በኋላ እንዴት ተመልሶ እርፍ ይዞ ወደ ኋላ ለማረስ ይሞከራል? የማይሆነውን የማይደረገውን ሲሠሩ ማየት ለተመልካቹም አስገራሚ ነው። ይህን የመሰለው ሲፈፀም አይዟችሁ በርቱ የሚሉ የሉም ማለት አይደለም። ወደ ተሳሳተ ጎዳና የሚመሩ መኖራቸውን እናውቅ የለምን? ለዚህማ መጽሐፈ መነኮሳት በከፍተኛ ደረጃ ምክሩን ይሠጣል። ጦሩን ታገሡ ሲል ምን ማለቱ ይሆን? የሰባት ሻለቃ ጦር ማለቱ እንዳልሆነ እንረደዋለን። ታዲያ ሚመት ሥጋዊ ጦር አይደለም የሚል ማን አለ? አሁን እኮ ሲሠራ የሚታየው ሊሆን የማይገባው ነው። ይህን አትሥሩ ይህን አታድርጉ ብሎ የሚመክር አባት ራሱ አታድርጉ የሚለውን ቃል ራሱ የሚሽር ከሆነ እንኳን ለሥራው ለጤንነቱስ ምን ማረጋገጫ ይኖረዋል? መልእክት ተቀባዩ ምዕመንስ ምን ዓይነት አመለካከትና ትርጉም ይሠጠዋል? አሁንም በካህን ስም ያልሆነውን የሥራ ጦር ታገሡ። በካህናት ስም የሚፈፀመው ደባ ይቁም። አበው እንደሚሉት «ነገር ሲያመልጥና ፀጉር ሲመለጥ አይታወቅም» ሆኖባቸው ነው እንጂ የካህናት ጉዳይ ከፍተኛ የአምባ መነጋገሪያ ጉዳይ ሆኗል።

አንድ ለጊዜው ስማቸውን ከመጥቀስ የቆጠብሁት ሰው ሥልጣነ ክህነት ሳይኖራቸው በድፍረት ካህን ሆነው ለማገልገል ሲጀምሩ ተገልጋይ ምዕመናን ከሚያዩትና ከሚሰሙት በመነሳት የክህነት ማስረጃቸውን እንዲያቀርቡ ሲጠይቋቸው የሠጡት መልስ ማስረጃዬ በግዕዝ ስለሆነ የቶጻፈው ግዕዙም ስለማይገባችሁ ተተርጉሞ እስኪመጣ ጠብቁ ነበር መልሳቸው። እነሱ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኑ መጻሕፍት ከቅዳሴ ጀምሮ በግዕዝ አይደል የሚነበበው ግዕዙንም ቢሆን ያቅርቡት ሲሏቸው የማይገባችሁን? ብለው ወደ ቁጣውና ወደ ዘለፋው ሲሻገሩ ማኅበረ ምዕመናኑ በጽሑፍ አሰናበቷቸው።
ይህ በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ የተፈፀመ ድርጊት ነው። ለእንዲህ ላሉ ካህናት እንኳን ለበላይ አባቶች ተጠያቂነት ሲኖራቸው ቀርቶ የቤት ኪራይ ለሚከፍሉት ምዕመናን እንኳ ተጠሪነታቸው በቂ ሆኖ አልተገኘም። ይህም ብቻ አይደለም። መቼም አሜሪካ ለገበያው ግርግር ሰዎች ምቹ ነውና የሌለ አንድ ትልቅ ካቴድራል በራሳቸው ፈጠራ ሠይመው የዚያ ታላቅ ካቴድራል ደግሞ የበላይ ኃላፊ ራሳቸውን አድርገው ለበታች ደብተሮች እንኳ ላልሆኑ ሹመት ይናኛሉ። ርእሰ ደብር ቀኝጌታ እያሉ በኅብረ ቀለም ያጌጠ ክርታስ አሳትመው ሹመቱን ይናኙታል። መቼም ይህ ሲደረግ የሹመት ያዳብርና ለመሰለው አገልግሎት በነፃ እንደማይሆን እንገምታለን። እንዲህ ዓይነት በስም የከበሩ በሥራ የከሡሩ ሰዎች ጥቁር ካባቸውን ደርበው ጥቁር ኩፋያ አጥልቀው ሲመሽ የሚወልቅ እሁድ እሁድና ሰው ባለበት አካባቢ ብቻ የሚጠለቅ በከተማው ሲኅማለሉ ይታያሉ። እኒህን የመሰሉ ብዙ ናቸው።

እንግዲህ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳድር መዘበራረቅ ያመጣው ግኝት ትክክለኛ ያልሆነ ምሥክርነት እየሰጡና እያስተማሩ ለችግሩ መፍትሔ ከመናገርና ከማቅረብ ይልቅ ማደናገሩን ሙያቸውና ተልዕኳቸው በማድረግ የችግሩ አባባሾችና አፅራረ ቤተ ክርስቲያን ሆነው አሉ ይኖራሉ። ለእንደነዚህ ላሉት የካህናት ካባ ተኀናጻፊዎች የበላይ የክህነቱ ባለቤቶች ግርግር የፈጠረውና ያስገኘው ምርት ይህን ይመስላል። እጅግ በጣም አስደንጋጭ ድርጊት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ የማታዝዘውና ያላከችውን ካህን መቀበሉና ለመገልገልም ሲባል ማስተናገዱ ለጊዚያዊ እንጀራ ተብሎ ዘስቄታውን ክርስቲያናዊ ሕይወት ማበላሸት ነው። ይህን ጊዜ ማን ይከላከል። ከማን ማስረጃ ይጠየቅ? ምዕመናን የመቆጣጠር የመከታተል ሙሉ በሙሉ የቤት ክርስቲያናቸው አደራ አለባቸው። ነገር ግን ምዕመናኑም ባንዳንድ ቦታ ቤተ ክርስቲያን የሚመሠርቱት ለአምልኮተ እግዚአብሔር ሳይሆን ለአምልኮተ መንግሥት ማለት ለድርጅታቸው ማጠናከሪያ



በገንዘቡም በሰውም ኃይል ምንጭነቱ ፍቱን ሆኖ በመገኘቱ ነው። ይህ መቼም ፀሐይ የሞቀው ሰው ሁሉ የሚያውቀው በገሀድ እውነት ነው።

የሚያሳዝነው ሁሉም ካህኑም የአሜሪካኑም ሲኖዶስና መሥራች ምዕመናንም ካንዳንድ ቦታዎች ተባባሪዎች በመሆናቸው ነው። በቀላሉ አነጋገር «ዚአከ ለዚአየ» [እኔ ላንተ አንተም ለኔ] ዓይነት ትብብር። ታዲያ ለዚህ ሁሉ ሽፋን ሆኗ መገልገያ የሆነችው ይችው ቅድስቲቷ እናት ቤተ ክርስቲያናችን ናት። አሜሪካ ደግሞ እንኳን እግዚአብሔርን ማምለክ ቀርቶ ለሠይጣን አምልኮም ከልካይ የለበትም። አሜሪካ የገባች ቤተ ክርስቲያን ምን እንበላት? እንደ ኢየሩሳሌሟ ምኩራብ የሚገርፍና ጠረጴዛዋን የሚገለብጥ ያውርድባት ብለን እንጸልይ? ከደረሰስ ያድርገው። እንግዲህ እንዴት አድርገን ጻድቃንን ከኃጥዓን እንለይ? ከዚህ ላይ ነው «ኩሎ ዐረየ ወኅቡረ ዐለወ።» [ሁሉም አንድ ሆነ ተባበረ ወነጀለ መዝ. 13:3 ] የሚለው ቃል ትርጉም የሚያገኘው። በዚሁ ዓይነትና መልክ የተቋቋመ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ነው።

ካህናት ሆይ እግዚኦ በሉ። እንከርዳድም ንፁሕ ስንዴም ያለው ከናንተው ዘንድ ነው። የአሜሪካው ሲኖዶስ ካህናትን ማቅለስ መነኮሳትን ማቆመስ ሥራው አልፎና ተርፎ ራስን በራስ መተካቱ ላይ ሆኗል ማለትም ኤጲስ ቆጶሳትን መሾሙን የድል መቀዳጃ አድርጎታል። ጳጳሳትን ማብዛት ማበርከት ለቤተ ክርስቲያኗ ብልጽግና ነውን? በሆነማ ምንኛ ደስ ባለን በነበር? ነገር ግን አይደለም። ባለመሆኑም ኃዘናችን ብዙ ድካማችን ጣር ጋር ሆኗል። ይልቁንም የሚያዝኑላትና የሚያለቅሱላት ለዓይናቸው እንቅልፍ ነሥተው ሌት ከቀን ቀሪ ሕይወታቸውን ነገ ከነገ ወዲያ በነጭ ከፈን ለምትጠቀለል ሥጋቸው ክብርና ልዕልና ከመሠጠት ይልቅ ለቤተ ክርስቲያናቸው ቢያውሉት እንዴት ባማረ? እንዴት በተዋበ? በነበር። ይህ ሲደረግ ባለማያታችን ደግሞ እጅግ በጣም አዝነናል።

የአሁኑን ፈጽሞ አያደርገውና ኢትዮጵያን በአንድነቷ ጠብቃ የኖረችው ቤተ ክርስቲያን ከማንነቷ ሥልጣን በጉልበት ተሠርዞ፥ ዘካሪዋ ተዘካሪ፥ መጽዋችዋ ተመጽዋች፥ ይቅርታ አድራጊዋ፥ ምሕረት ጠያቂ ሆናለች። ገፀ ላሕይዋም ሆነ ግብሯም ከስሞና ገርጥቶ እንዲሁም ተለውጦ ይታያል። ይህን ለማለት የፈለግሁት የካህናት መልካምና ቅን ሥራ ወዴት መሄዱንና በምን መልኩ መተካቱን ለማሳየት ነው። ካህናት ጠባ ለኪዳን መሸ ለቁርባን እየተባሉ የአገልግሎታቸውን ዘርፈ ብዙ መሆኑን ይህን በመሰለው

ፖለቲካዊ ኩባንያዎች ናቸው። በሃይማኖት ስም የግል ንግድ የሚያካሂዱ የፖለቲካ ሥራ የሚፈጽሙ ናቸው። ዛሬ የውጭ ሲኖዶስ ሲኖር ማኅበረ ካህናቱ ሥራውን ጨርሶ ተበትኗል። ሠርሆተ ማኅበራት ተደርጓል። ስንብት አድርገዋል ማለት ነው። አሁን በሰሜን አሜሪካ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሲቲያን ተከታዮች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ።

አንደኛው ከእናት ቤተ ክርስቲያን ተመርጠው የተላኩ ካህናትና ጳጳሳት ሥር የሚገለገሉ፥ ሁለተኞች አሜሪካ ባለው ሲኖዶስ ሥር ያሉና ካህናት ከአዲስ አበባ በእነሱ በኩል የመጡ ወይንም ከዚህ ሙያው ያላቸውን መቀደስ ማወደስ የሚችሉ፥ ሦስተኛዎቹ ከእናት ቤተ ክርስቲያንም ሆነ አሜሪካ ካለው ሲኖዶስ ሥር ያልሆኑ ገለልተኞች የሆኑ በራሳቸው በጎ ፈቃድ የሚመሩ ናቸው። እንዲህ ያለ ዝብርቅርቅ ብሎ የሚገኝ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና ምስረታ ላይ ናት ቤተ ክርስቲያናችን። እኚህ ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉት ኢትዮጵያውያንን ብቻ ነው። ምናልባት አንድ ወይንም ሁለት ቤተክርስቲያኖች ብቻ በእንግሊዝኛ ለካረቢያንና ለመሳሰሉት ክርስቲያኖች አገልግሎት የሚሠጡ አሉ። እንግዲህ ይህ ፀጋና ሀብት ከሆነልን እሺ በጎ ግን አይደለም እጅግ በጣም የሚያሳዝን የሚያስለቅስ በእውነት ኢትዮጵያውያን እንዲህ ነን የሚያሰኝ ነው። ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ቤተ ክርስቲያናችን ይህን በመሰለ መልኳ ትገኛለች። ሥዕለት ለሚሰሙ ታቦታት አንድ እንዲሆኑ ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ጋር እንዲደባለቁ ተሳሉ ጸልዩ ከልብ እንባ አፍሳችሁ ለምኑ። ሰው የሚፈታው ጉዳይ አልሆነም። ሁሉም ለራሱ እንጂ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚያስብ ጨርሶ ፈጽሞ የለም። እንዴት እጅግ በጣም የሚዘገንን ነው። እንዴትስ የሚመር ነው። ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በሠጡ አባቶችና ካህናት በዚህ ዓይነት ቂም በቀል ለብሰው እንዴት ወደ ሥጋ ወደሙ ፍትታ ይቀርባሉ? እግዚአብሔር ሆይ ፍርድህን ስጥ። ዳታንና አቤሮንን ያስጠምህ፥ ሰዶምና ገሞራን ያቀጠልህ፥ ምነው ምሕረትህ በዛ? ስምህን መቀደሻና መወደሻ የሆነችውን ይችን ቤተ ክርስቲያን ከሚያጎሳቁሏት ዕጅ አታወጣትምን? ይህ የደጋጎች የምዕመናን ኃዘንና የዘወትር ጸሎትና ጥያቄ ነው።

አበው ካህናት እናንተም ተመስግናችሁ፥ ሕዝበ ክርስቲያኑንም አስደሰታችሁ፤ በኖራችሁ በነበር። እስከ መቼስ ድረስ ነው በዚህ ሁኔታ የምትቀጥሉት? ወይ ከዚህ አልሆናችሁ፥ ወይ ከዚያ አልሄዳችሁ። እንዲሁ ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ፥ ከወዲያ ወዲህ



እየተወዛወዛችሁ በተፈጥሮአችሁ የሌለውን ተግባር ታከናውናላችሁ። ለዕለት ጉርስ ለዓመት ልብስ ብላችሁ የዚችን ጥንታዊት ልዩና ብርቅ ድንቅ ቤተ ክርስቲያን የፀጋ የበረከት ቦታ ራቁት ታስቀራላችሁን? አለቡበት ራሳችሁን መርምሩ። ይህ የምትፈጽሙት ሥራ የካህናት ባሕርይ አይደለምኮ! «ኩኑ ጠቢባነ ከመ አርዌ ምድር ወኩኑ የዋህነ ከመ ርግብ» [እንደ እባብ ብልሆች እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ] ለምኑ ይሆን? የዚህ ቃል ትርጉም ምንድን ነው? ጥበባችሁስ ወዴት አለ? የዋሕነታችሁሳ ወዴት ነው?

ይሁንና እንደሚታወቀው ቀራንዮ ቀራንዩ መድኃኔ ዓለም መድኃኔ ዓለም ካህናቱ ካህናቱ ብለን እንሻገር። የበደላችሁት ራሷን በእንተ ስማ ለማርያም ብላችሁ ያስተማረቻችሁን አንዲት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ነው። አባቶችስ ሥልጣናችንን ተነጥቀናል ብለው እሱም ቢሆን ነፍስንና ሥጋን አንድ ያደረገ አምላክ ያውቀዋል። ያያቸዋል። ለመሆኑ በትውልድ በሥርዎ ክህነት የወረሱት ርስተ ክህነት ነውን? እነሱን አርዓያ አድርጋችሁ ቤተ ክርስቲያናችሁን መበደሉ ይብቃ በሉት። ሁሉም ያልፋሉ እናንተም ታልፋላችሁ ባላችሁ ጥቂት ጊዜ ሥራ ሥሩባት። ትላንት የነበሩ ዛሬ የሉም። ለእናንተ ምኑስ ይነገራል? ነገር ግን እወቁበት።

አሁን ያለወቅቱና ያለመከሩ በዘነበው ዝናም የቤተ ክርስቲያኗ የአንድነት አዝመራ አልተበላሸምን? ያለ ጥቅም አልቀረምን? የሰዎች ምስክርነት ግን እንዳልሆነ ሆኗል። ነገር ግን የኔ ጥያቄ ቤተ ክርስቲያኗ ጠላቶቿ ከበዋት፥ ጥጓት ማታ ናዳ እየፈነቀሉባት ባለበት ወቅት የሚጠበቀው ምንድን ነው? ይኸውና የፕሮቴስታንቱ ራዲዮኑ፥ ቴሌቭዥኑ ጣላት ግረፋት እያሏት አይደለምን? በስሟ መባረክና መቀደስኮ ሊታጣ እንደሚችልም ከሩቁ መመልከት ይገባል። ያ ካልሆነ የካህንነቱ ንጽሐ ባሕርይ የቱ ላይ ነው? ዓይናችንን ከፍተን እንመልከት። ይህን በማያደርጉት ላይ የተሠጠ ምሳሌም አለ። ለግንዛቤ ያህል እንዲህ ይላል። «አንድ ንብ ከምትሞት ሃምሳ ካህን ቢሞት ይሻላል።» ካህናት እዕይንተ እግዚአብሔር እየተባላችሁ መጠራታችሁን አትርሱ። አሁን ግን የእግዚአብሔር ዓይኖች መሆናችሁ በነበር ካልተያዘ በሥራ አታሳዩትም። ስለዚህ ካህናት ዘበምድር ብለናችኋል ብለን እንውጣ። የምሕረት፥ የይቅርታ፥ የሰላም ዓይኖቻችሁ ይብሩ ይገለጡና ችግሩን ይመልከቱ። ማኅበራችሁ የአድማ መበተኛ፥ ከሠይጣናት ቁራኛ ፈጽሞ መዳኛ ይሁን። ለሁሉም ጊዜ አለው። የምስክርነታችሁ ጊዜው ዛሬ ነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንዳሉት «በጊዜ ሥሩበት እንጂ ጊዜ አይሥራባችሁ።»

# ፫ . የሠበካ ጉባዔ

ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባል በመሆናችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ። ቀደም ሲል የነበራችሁ አሁን ግን በልዩ ⁄ ልዩ ችግር የተሰደዳችሁ ኑ ተመልሳችሁ። ቤተ ክርስቲያናም ዕጇን ዘርግታ ትቀበላችኋለች። ምዕመናን ሆይ! ሃይማኖት በአንድ በእግዚአብሔር ማመንና የመንግሥቱ ወራሽ፥ የስሙ ቀዳሽ መሆን ነው። ሃይማኖት ከሰብአዊ አስተሳሰብና አመለካከት እጅግ በጣም ልዩ ነው። ሲሞቀን የምናወልቀው፥ ሲበርደን የምናጠልቀው አይደለም። እንዲሁም ስናዝን በልቅሶና በእንጉርጉሮ፥ ስንደሰት ደግሞ በክበሮ የምንፈነጥዝበትም አይደለም። ሃይማኖት የማንነት መለኪያ የእግዚአብሔር መገለጪያ ማወቂያና መገዣ የራሱ የባለቤቱ ስም ነው። አዎ! ሰው በተፈጥሮው ነፃ ነው። የፈለገውን ይይዛል የማይመስለውን ያስወግዳል። ሲጠይቅ ያገኛል። በር ሲያንኳኳ ይከፈትለታል እንጂ ሲርበው አምላኩ የሚያጎርሰው፥ ሲጠማው ውሀ በብርጭቆ ቀድቶ የሚያጠጣውም አይደለም። ስጠኝ ሲል ግን ይሠጠዋል። ይህ ደግሞ እንግዲህ የሚያመለክተው ሰው በራሱ በጎ ፈቃድ የሚመራ መሆኑን እንረዳለን።

ከዚያም በላይ እግዚአብሔርን ዘወትር የሚያመሠግኑ፥ የእሱን ምሕረት ለሚሹት፥ የሥራውን ቅደም ተከተል ይገልጽላቸዋል። ከእነዚህ ሕዝብ መካከልም ኢትዮጵያውያን ይገኛሉ። ሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ የታወቀውና የተጀመረው በኢትዮጵያውያን እንደሆነ ታሪክ ያስረዳናል። ከዚያም አልፎ ተርፎ ክርስትናም ሲገባ በራሱ ፈቃድና ተአምራታዊው ሥራው ነው። ዘወትር ሊታወሰን የሚገባው ዓቢይ ምሥጢር ቢኖር ይህ ክርስትናን በከፍተኛው ኢትዮጵያዊው ሹም በባኮስ ወይንም በጃንደረባውና በራሱ ደቀ መዛሙርት አማካይነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሠበክ ማድረጉ ነው። ክርስትና በኢትዮጵያ የተሠበከው በእግዚአብሔር በራሱ ጥበብና ፈቃድ ነው። ከዚያች ቀንና ሰዓት ጀምሮ ያለችውና የኖረችው ይችው የኦርቶዶክሷ ሃይማኖታችን ናት። እነሆ ከቁልኬዶኑ ጉባዔ ጀምራ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተብላ ጸንታ ትኖራለች ትታወቃለችም።



ይችን ሃይማኖት፥ ይችን ቤተ ክርስቲያን በሰይጣናዊ ቅናት ለመገልበጥና ለማፍረስ በየዘመናቱ ከሰብከቱና ከውትወታው ከፖለቲካውና ከዲፕሎማሲው ሁሉ ባሻገር የጦር መሣሪያ ታጥቀው፥ ሠራዊት አሠልፈው ወረዋት ነበር። ግን እንኳን ሊያጠፏት ይቅርና ከመሠረቷም አልነቀነቋትም። ምክንያቱም በራሱ በኢየሱስ መሠረትነት፥ በራሱ በጎ ፈቃድ ላይ የተመሠረተች ናትና ነው። ይችን ቤተ ክርስቲያንም በመንከባከብና በመጠበቅ ያላቸውን በመሥጠት አብያተ ክርስቲያናትን በማነጽ ዋናው የመሠረቷ ደጋፊዎች ሆነው የኖሩት አሁንም ያሉት ምዕመናን ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ያለ ምዕመናን ምዕመናን ያለ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሌለው አካል ነው። እንዲያውም ራሳቸው ምዕመናን ናቸው ቤተ ክርስቲያን የሚባሉት። ያለ ቤተ ክርስቲያን ካህን ብቻውን ምንም የሚሠራው ነገር የለም። አገልግሎቱም ለምዕመናን ነውና ነው። ይህም ምዕመናን ምን ያህል ከፍተኛ ቦታ እንዳላቸው ያረጋግጣል።

ይህን የካህናትና የምዕመናን ጉባዔ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዕጅና እግር ራስና እንደበት ዓይንና ጆሮም ነው። ይህ የሠበካ ጉባዔ ባይኖር ባይቋቋም ኖሮ ቤተ ክርስቲያናችን ምን ትሆን ነበር? ምንስ ይውጣት ነበር? የትስ ትገባ ነበር? ምዕመናን ነገሩን በሃይማኖት ዓይን ተመልክቱት ዕዩት። ይህ የሠበካ ጉባዔ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በፀሐይ ግባት ሲከለል የሚመጣውና የሚተካው ጨለማ ሌሊት ነበርና ይህን አስቀድሞ በማሰብ በቀን ገና ሳይጨልም በመቅረዞች ሁሉ ዘይት መሙላት አስፈለገ። ይህም ቤተ ክርስቲያኗ በጨለማው እንዳትሰነካከል ያለ ብርሃንም በጨለማው እንዳታድር ከተኛችበትም እንዳትቀር አድራ እንድትነሣና እንድትውል ተዘጋጀላት። ይህም የመቅረዝ ዘይት ተብሎ ለቤተ ክርስቲያኗ የተዘጋጀው የሠበካ ጉባዔው ነው። በዚህም የሠበካ ጉባዔ ምዕመናን ሕጋዊ በሆነ መንገድ በነጋሪት ጋዜጣ አንድ ድርጅት አሉም የሠበካ ጉባዔ ተቋቋመ። ይህን ጉባዔ ሕጋዊ የሚያደርገው ቃለ ዓዋዲ በአዋጅ በመንግሥት ፈቃድ ተቋቋመ።

ይህ የሠበካ ጉባዔ መመሥረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በሮች በጨለማው ተዘግተው እንዳይቀሩ ከመዘጋት አዳነ ጠበቀ። ይህን የሠበካ ጉባዔ እንዲቋቋም የአወጀና ያጸደቀ መንግሥት ሲፈፀም የሚቀጥለው መንግሥት ከግለ ሰብ እስከ ቤተ ክርስቲያን ሀብት ንብረት በሙሉ ወረሰ። ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት የምታገኘው የዓመት በጀት በከፍተኛ ደረጃ ቀነሰ ተቋረጠ። ገዳማቱና አድባራቱ መተዳደሪያ አጡ ነጡ። በዚያን ጊዜ

ይሁንና በገጠር ያሉ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ኑሮ ግን ገና እንደቀጨጨ ነው። በተለይም የአብነት ትምህርት ቤቶች እጅግ ተዳክመዋል። ይህ በውጭ የሚገኘው ሕዝበ ክርስቲያን ከእናት ቤተ ክርስቲያኑ ጋር አንድ ሆኖ ቢሠራ ኖሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መላ አፍሪቃንም አዳርሳ በነበር። የሰው ልጅ አፍ መፍቻ የሆነውን የግዕዝ ቋንቋም በተለይ ለአፍሪቃውያን የስማቸው መጠሪያና መጸፊያ እንዲሆን ባደረገችና ባዳረሰች በነበር። ነገር ግን ለመልካም ነገር ሁሉ መሰናክሉ ብዙ ነውና ቤተ ክርስቲያኗን በፖለቲካው ካባ አሸፋፍነው ማስፈራሪያ አደረጓት።

እንደ ቀደሙ አባቶች ቢሆን ነገሥታትን ቀብተው ቃለ መሐላ አስፈጽመው ያነገሥዋቸው ስለነበር ይህን አትሥራ ይህን ተው የማለቱ ሥልጣኑም ኃይሉም ነበራቸው። ዛሬ ከደርግ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ቀብታ ማንገሥዋን ተቀምታ ተቀምጣለች። ታዲያ በሌላት መሣሪያ እንዴት ትዋጋ? እንዴትስ ታድርግ? ካህናቱም ምዕመናኑም የቤተ ክርስቲያኗ ክብር ይመለስ ብለው አልተጉም። ነገሥታት ቀብተው እንዲያነግሡ ኃሳብ እንኳን አልሠጡም። ያማ እንዳይሆን ደግሞ የመንገሡን ድርሻ ሁሉም በተራ ለማግኘት ተሠልፎ የሚጠባበቀውን ፖለቲከኛ ማስቀየም ሊመጣ ነው። የፖለቲከኛውንና የድርጅቱን ብዛት ስንመለከት እንኳን ባሉት ሰዎች እድሜ ሊደርስ ቀርቶ ሰባት ትውልድ ላይ እንኳ አይደርስም። ለሁሉም ሥልጣን ይዳረስ ቢባል እንኳን ወርና ዓመት ሰዓትና ቀን እንኳ አይበቃም።

ታዲያ ምን የዕጅ ማስገቢያ ቤተ ክርስቲያኗ አላት? የሥልጣን ርክክብና ሽግግር ከነበረው ሕግና ሥርዓት ወጥቶ ባለበትና ሥልጣን በጉልበት ተወስዶ ታውጆ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ተፋተዋል ተብሎ በአዋጅ የጸደቀውን ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን በሌላት ቀትር ርግማን ውግዘት አላደረገችም ብሎ ማብጠልጠል ለመሆኑ ትክክል ነውን? አድርጊስ ብሎ መምከር ራስ ወዳድነት አይደለምን? አሜሪካ ሆኖ ስለ ኢትዮጵያ መናገርና መተቸት ዱባና ቅል አበቃቀላቸው እየቅል መሆኑን ያለመረዳት ነው ያሰኛል። ወይንም በሞኝ ዕጅ የእባብ ጉድጓድ ይለኩበት ሲሆን ነው። ይህን የመሰለውን ሥጋዊ አስተዳደርማ እናንተ የነበረውንና ለብዙ ዕልፍ ዓመታት ጸንቶ የኖረውን የመንግሥት ሥርዓት በኀብረት ንደን ያመጣነውና ያፈራነው ስለሆነ ራሳችን እንመገበው እንጂ ሥልጣኗን ማዕርግ ሠሞነቷን ከቀማን በኋላ በሌላት ሥልጣን መንግሥት አደላድይ ብሎ መውቀሱ ሃይማኖታዊም ሰብአዊም



አስተሳሰብ አይደለም። ለቤተ ክርስቲያኗ ቃል ግቡላትና ወደ ቅድመ ሥልጣንሽ እንመልስሻለን በሉ ካህናቱም በጉዳዩ ይተባበሯችሁ። ያለበለዚያ ግን ነፃ አገልግሎት ከማይሰጥበት አገር ተቀምጦ ነፃ አገልግሎት አልተሠጠም ማለት ትክክለኛ አባባል ነው ማለት ይከብዳል።

እንግዲህ እንዲያው ለፖለቲከኞች የማይሆነውን ይሆናል ብሎ መናገር ይቀል ይሆን እንደሁ እንጂ ለቤተ ክርስቲያን ግን አዎ አዎ አይደለም አይደለም ነው አመክሮዋና አስቡላት። ከመንገድ የተገኘውን ድንጋይ ብቻ እያነሡ መወርወር የሚወድቅበትን ያለመመልከት በሰው ራስ ላይ ያርፍና ሰው ይጎዳልንን ከውርወራው ጋር አብሮ ማሰብ ነው። እስካሁን የፈለጓትን አሞራ ዥግራ ናት ብሎ መብላት ስለሆነ የፖለቲካው ጥበብ በዚያ አልተባበርሺም ብሎ ቤተ ክርስቲያኗን መውቀሱና ማዋረዱ ራሱ በቅድሚያ የሚሠሩትን ያለማወቅ ነው። በሃይማኖት ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ኃጢዓት የሚባለው እኮ በፖለቲከኞች ዘንድ ጽድቅ ነው። የፖለቲካ ሥራ ከሐሰት የጸዳ አይደለም። ታዲያ በሐሰት አትመስክር ብላ ከምታስተምር ቤተ ክርስቲያን ጋር እንዴት የመዝገበ ቃላቱ ትርጉም አንድ ሊሆን ይችላል። ቤተ ክርስቲያን ስትጸልይ ከጻድቃን ይልቅ ለኃጥዓን ስለሆነ የጸሎቱ ተጠቃሚዎች እነማን እንደሚሆኑና መሆናችሁን ግን ልትገነዘቡት ይገባል እላለሁ።

ይልቁንስ ከዚህ ላይ በአሜሪካ ያሉት አባቶች ለብቻቸው ጎጆ መውጣቱን ርግፍ አድርገው ትተው ወደ አንድነቱ ወደ ሰላሙና ፍቅሩ ቢመጡ ስንት ታምር በተሠራ በነበር። ነገር ግን በገዳመ ቆሮንቶሱ የፖለቲካ አሳሳቾች ሰንሰለት ታሥረው ከተራራው ላይ ራሳቸውን ወርውረው መንግሥትና ግዛት የሚያሰጥ ሥራ እየፈፀሙ ነው። በገዳም የነበረ ሰው ከገዳም ወጥቶ ምን የሚያሠራ ነገር ነበር? ብፁዓን አባቶች ለዚህ ሕዝበ ክርስቲያንና አገር ስትሉ አሁንም ልዩነት የመናፍቃን ሥራ ነውና እባካችሁ ርግፍ አድርጋችሁ ተዉት። ቤተ ክርስቲያናችንን እንገንባ የአብነት ት/ቤቶችን እናድስ። ይህን ብታደርጉ ሕዝብም የቤተ ክርስቲያኗም ታሪክ ሲያወድሳችሁ ይኖራል። ይህን ባታደርጉ ግን ትውልድና ዘመን ሲያዝንባችሁና ሲወቅሳችሁ ይኖራል። የእግዚአብሔርን ቤት በሁከትና በነውጥ ትመሩታላችሁን? እግዚአብሔር አይወደውም። ወደ ማኅበራዊ ኑሮውና ጸሎቱ ተመለሱ። እኛንም ደስ ይበለን። በቂም በቀልና በጥላቻ የእግዚአብሔር ቤት አይገነባም። እኛንም ያለንበትን ዘመንና ጊዜ እንደ ኢዮብ አታስረግሙን።

ይህን ሳንሠራ ብንቀር እንደ ኃጢዓት ይቆጠርብናል። ታሪክም ይወቅሰናል። ክጽድቅ ይልቅ ኩነኔ ይጠብቀናል። ይህን አሁኑኑ እናስተካክል። ክሁላችን የሚጠበቅ ዓቢይ ተግባር ነው። ይህን ባለማድረጋችን የታሪክ ጠላቶቻችን የራሳችንን ልጆች አሠልጥነውና አስታጥቀው፥ በየመደሩና በየሠፈሩ እየገቡ፤ በዝግ ቤት ውስጥ ከሚፈጽሙት ደረቅ ወንጀል ኀልፈው ተርፈው፥ ቀን በቀን፥ በራዲዮ፥ በቴሌቪዥን ሁሉ ታላቅ ዘመቻ እያደረጉብን ነው። ይህን የጦር ሠራዊት ትጥቁን እናስፈታው። ለኛ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን፤ ሃይማኖታችን አገራችን፤ አገራችን ሃይማኖታችን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው።

ይህ በእንዲህ እንዳለም ወጣቶቻችንን ከቤተ ክርስቲያናቸው ጋር እንዲውሉና እንዲያድሩ እናድርግ። በየቦታው አዲስ በመጣው ሃይማኖት ሁሉ እየገቡ እየተሰነካከሉ ነው። ወጣቶቻችንን ማጣት ማለት የአትክልት እርሻዎቻችን ያለ ፍሬ ቀሩ ማለት ነውና እጅግ ከፍተኛ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባናል። አሁን ብዙዎቹ በየቦታው ሲባዝኑ ይታያሉ። እንኳን ወላጅ ያላቸው ናቸው ብሎ ለመናገር ይቅርና ከኅብረተሰቡ ጋር ይኖራሉን ያሰኛል። ልንጠነቀቅላቸውና ፈጽሞ ልንከባከባቸው ይገባል። እኛ ወላጆች ልንመክራቸውና ልንቆጣጠራቸውም አስፈላጊ ነው። ደግሞም ፈጽሞ ማድረግ ይገባናል። ያለበሰዚያ ልጆቻችንን ከአገራቸው ታሪክና ሃይማኖት ነቅለን ጣልናቸው ማለት ነው። ምንም የምናወርሳቸው፥ ጊዚያዊ ሀብት ንብረት፥ ርስት፥ ባድማ፥ ባይኖረንና ብንቀማም ቢቻል እኛው ካልቻልን ራሳቸው ከዘንዶው አፍ ፎልቅቀው የመውሰድ ኃይል ስላላቸው እነሱን ማዘጋጀት የግዴታ ግዴታችን ነው። ከዚያም ባሻገር የወላጅና የሃይማኖታዊ አደራ አለብን። ዓይተን እንዳላየን ሰምተን እንዳልሰማን መሆን ፈጽሞ አይገባንም። በዚህ ከቀጠልን የወላጅ መካን ሆን ማለት ነው።

ሌላው በስፋት የሚታየው በተሰይም በውጭ ያለነው ምዕመናን ክርስትና ለማስነሳት፤ በተክሊል ጋብቻ ለመፈፀምና ለጸሎተ ፍትሐት ስንል ብቻ ከቤተ ክርስቲያን ከመሄድ በስተቀር የቤተ ክርስቲያኗ ችግር ምንድን ነው? ይህ ቤተ ክርስቲያን በማን ይመራል? ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ጠብቆ በሊቃነ ጳጳሳት ተባርኮና ተመርቆ የተቋቋመ ነውን ወይንስ እንዲሁ አገልግሎት ብቻ ስለሚሠጥበት ዘው ብሎ ገብቶ፥ ዘው ብሎ መውጣት ነው? እንግዲህ ምዕመናን ልጆቻችንን ክርስትና እንዲነሡልን ማድረጋችን የተቀደሰ ሥራ ነው። ነገር ግን አገልግሎቷን የመፈለጋችንን ያህል አብረንም የቤተ ክርስቲያኗ ችግር ተካፋይ የመሆን ግዴታም አለብን። እኛ



ከተባበርን፥ እኛ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፥ እንደ አንድ ልብ መካሪ ከሆን፤ የጎደገደው ይሞላል። የጎበጠው ይቀናል። ባድማዋን ጥላ የተሰደደችውም ሰላም ወደ ቦታዋ ትመለሳለች። ቤተ ክርስቲያናችንም በጽኑው ትጠነክራለች። ወጣቶቻችንም ከቤተ ክርስቲያናቸውና ከወላጆቻቸው ጋር አብረው ያድጋሉ። የማንነታቸው ወራሾችና ተተኪዎችም ይሆናሉ።

ሁላችንም እንደምናውቀውና የበይ ተመልካች ሆነን ያሰንበት ብሔራዊው አንድነታችንና ማንነታችን ድሮ ጥንት በውጭ ወራሪዎች ነበር የሚፈተነውና የመናድ ሥራው የሚከናወነው፤ አሁን ግን ተለውጦ፥ መልኩንም ቀይሮ፥ በኛዎቹ በመልክም፥ በቋንቋም፥ የሥጋችን ቁራጮችና የአጥንታችን ፍላጮች በሆኑት ነው። «ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል» እንደሚባለው የሃይማኖት ደላላዎች ከበዙበት ዘመን ላይ ነን። አዎ! እኛ ሃይማኖትን ገዝተንም ሸጠንም አናውቅም። ያለ ውጣ ውረድ በራሱ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት የሰው ልጅ በምድር መንቀሳቀስ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እሱን ፈልገን እንድናገኘው አድርጓል። አውቀነውም ስናመልከው ኖረናል። አሁንም አለን። ግን አሁን እርሱን ትተን ማንን እንድናመልክ ነው ገንዘብ የሚሠጠው? የሃይማኖት መሰወጫ ገንዘብ ይከፈል ጀምሯል። በገንዘብ ሃይማኖቱን የለወጠ ሰውስ ምኑ ታማኝ ይሆናል? እንዲሁ በዚህን ያህል ገንዘብ ይህን ያህል ሰው ገብቷል ብሎ ከመናገር በስተቀር እንዴት አማኝ ሊሆን ይችላል? ኢትዮጵያዊ እኮ ሃይማኖቱን በገንዘብ አይሰውጥም። ራሱን የማያውቅ ካልሆነ በስተቀር እንኳን በገንዘብ በሠይፍና በካራም አይሰውጥም። አንገቱን አስቆርጦ ዓይኑን አስፈርጦ ለሃይማኖቱ ተፋጥጦ ኖሯል። ማንነቱንም አስመስክሯል። ይሁን እንጂ አሁን ገንዘብ ይዘው አማኝ ለማደን ለተሰሰፉት ሰዎች አዝናለሁ። በገንዘብ ሲገዛና ሲሰወጥ የምናውቀው የሚታረድ በግ ፍየልና በሬ እንጂ ሰውስ ሰምተንም አናውቅ። አይመጣ ጉድስ አለ? ተራው ስብከት ባዶ እየሆነ ሚዛን አልደፋ ሲል በጥራ ገንዘብ ገቡበት። ያን ገንዘብ የሠጠ ጌታ የሚነሣበት ረጅምም ዕጅ እንዳለው ያሰመገንዘብ ነው። አማኝ ከሚገዙበት ትምህርት የሚቀስሙበት ት/ቤት አይሠሩለትምን? ቢሆን እንኳ እነሱ እኮ የሚገዙት ሥጋውን እንጂ ነፍሱን አይሆንም።

የሚገርመው ደግሞ በክርስትና ስም ጳንጤው ነው ያስቸገረው። ለምን የኛን ትተን የእነሱን እንድንይዝ ይወተውቱናል? እኛን መንግሥተ ሰማያት ለማስገባት አዝነውልን ነውን? ይመስላችኋል? አይደለም። ያስ ቢሆን እንዲህ በዕጅ በእግራችን እየገቡ ባላስቸገሩንም በነበር። ደግነት መሥራት ቢፈልጉ ኖሮ

ወድቆ ለሚለምነው ሰው መጠለያ ሠርተው፥ ባላቸው ገንዘብ የዕለት ምጽዋት መሥጠት ሳይሆን ሠርቶ የሚኖርበትን ድርጅት በፈጠሩለት በነበር። በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ እንዲሉ የባሰውን ከአሥር አንድ ያገኛሃትን አምጣት ትፋት ይሉታል። ምነው ታቦት አያስፈልግም ብለው ከሚለፉ ለምን ከአሥር አንዱ መዋጮዋ ትቅር ብለው አልሠበኩ? ይህምኮ የኦፊት ሕግ ነው። ከአሥር አንድም ታቦቱም ከኦሪት የወረስናቸው በእምነቱ የነበርንበቱ በመሆኑ ያገኘነው ነው። ትላንት ከትናንትና ወዲያ እንደናንተ ያወቅነውና የተረዳነው አይደለም። እናንተ በድብ፥ በዘንዶ፥ በጨረቃና በከዋክብት በተራራና በዛፍ ያመልኩ ከነበሩት ሰዎች ቅጥረኞች በመሆናችሁ እንጂ ማንነታችሁንማ ብትረዱ ኖሮ ይህን ባላደረጋችሁ በነበር።

እንግዲህ ከተዘረጋው መጋረጃ ውስጥ ያለውን ኢትዮጵያን ለማረድ ከተጋደመው ሃይማኖታዊ ፖለቲካዊ ካራ ውጭም ይበላው ያጣ፥ ሰውነቱ የገረጣ፥ ይህን ደሀ ሕዝብ ጌቶቻችሁ በኢየሱስ ስም ይበዘብዙታል። እኛን ግን ዝክርት፥ ተዝካርና ስንበቴ ያስደግሱታል ይሉናል። ያውም የደረሰውና የተራበው መንገደኛ ሁሉ የሚበላውን ምግብ እንደ ኃጢዓትም ቆጥረውብን። የእነሱ መዋጮ ግን የሚሄደው ወደ አንድ ጎተራ ብቻ ነው። ይህን ጉድ ተመልከቱት።

አንድ ጊዜ የአክሱም ጽዮን በዓል ሲከበር በ1966 ዓ. ም. እንደ አጋጣሚ ከቦታው ተገኝቼ ነበር። በዚያን ጊዜ የትግሬ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ትምህርት ሲሠጡ ያሉትን ማውሳት ፈለግሁ። «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከምሁራን ያልተራቆተችው በሕዝቡ ደግነትና ቤተ ክርስቲያኗም ተማሪ ቁራሽ ፍለጋ ሲመጣ ምዕመናኑ የመዘከር ግዴታ እንዳለባቸው በማስተማሯ ነው። ይህን ትምህርትም ሕዝቡ በተግባር የሚያውቀውና የለመደው በመሆኑ እንደ ብሔራዊ ግዴታው ቆጥሮት እነሆ እስካሁን የሃይማኖቱ ዓምድ የሆኑትን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሲያፈራበት ኖሯል። ለዚህ ዓቢይ ሥራ እንደ ምሳሌ የምጠቅሰው የጎጃምን ቤገምድርና የሰሜንን የሸዋን የወሎንና የትግሬን ሕዝብ ነው። እኔ ራሴ በዓይን ምሥክርነት ነው የምናገረው። በጎጃም ተማሪ ከበር ሲቆም ሥራ ውላ ገና ምጣድ ሳትጥድና ሳትጋግር የደረሰባት እንደሆነ ተሜ ተመልሰህ ና ገና ምጣድ እየጣድሁ ነው ትለዋለች። ተመልሶም ሲሄድ ያልተቆረሰ ትኩስ እንጀራ ትዘከረዋለች። ይህ አሠራር እነሆ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ምሁራንና አባቶችን አስገኝቷል።» ብለዋል።



ዛሬ ይህን ብዙ ምሁራንን ያፈራውን ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነው የኛዎቹ ቹልችላዎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ዝክርት ለመቃወም የተነሡት። የተቃውሞ ማስነሻ እንጂ ከላይ እንደ ገለጽሁት ቤተ ክርስቲያኗን ለመሸርሸር ምክንያት ማብዢያ ነው። የእውነት አስተማሪዎች ቢሆኑማ ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ የሚታደለው ሕዝብ፥ ለጧት ቁርስ፥ ለቀን ምሳና ለማታ ራት የሌለው መሆኑን ከማንም የበለጠ ያውቁታል። ይህን ቢተመለከተ ምን ያደረጉለት ጉዳይ አለ? ኢየሱስ እኮ የተራቡትን መግቦ፥ የታመሙትን ፈውሶ ነው ያስተማረው። በፈላ ጎጆ አዳራሽ ደሃውን ሕዝብ ሰብስቦ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አዒላት የሆናችሁ ጨለማ ውስጥ ነው ያላችሁ። ዛሬ ለመዳን ትሻላችሁ? በኢየሱስ እመኑ ይላሉ። ኢየሱስን የማያውቁት ይመስል? ዘመኑ ቡድንና ድርጅት መፍጠር በቀላሉ በድምጽ ብልጫ ተብሎ ትላንት በአገራችን ላይ የደረሰውን እንደተገነዘብን ነገ ከነገ ወዲያ ሳይሆን ከአሁኗ ሰዓት ጀምሮ ደግሞ ቤተ ክርስቲያናችንን ለመናድ ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ክተዳከመች የእነሱ ሚሺን ግብ መታ ማለት ነው።

ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ሆይ! ሰው በሕይወቱ ውስጥ ለአገሩ ደኅንነት፥ ለሕዝቡ ዕድገት የማያደርግ ከሆነ ሰው በእውኑ ለምን ተፈጠረ? «ቦኑ ለከንቱ ፈጠርኮ ለሰብእ» እግዚአብሔርስ በእውኑ ሰውን ለከንቱ ፈጠረውን? ከቅድመ ልደተ ኢየሱስ ክርስቶስ ጀምራ በእግዚአብሔር እምነት ጸንታ የኖረችውን አገር ዛሬ በጠርነት ያጡትን ወረራ በሃይማኖት ስም ለማግኘት ስለሆነ ይህን ተንኮል በጋራ ልንቋቋመው ይገባል። ይህ ደግሞ የሁላችንም ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ግዴታችን ነው። በእውኑ ለምን ዛሬ ሃይማኖት እንደ ድርጅት ተከታዮቹን በገንዘብ መግዛት አስፈለገው? ዛሬ ተበልቶ ነገ ለማይደገም ዳቦ ብለን ለዘለዓለም በልጆቻችንና በአገራችን ላይ መከራ ጥለን አንለፍ። የዛሬ ቀልድ፥ የነገ ፀፀትና የእግር እሳት መሆኑን ለአንዲት ኬክሮስ [ሴኮንድ] እንኳን ችላ ማለት የለብንም። ይህንን ግንዛቤ ውስጥ አስቀምጠን አገራችንንና ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።

ፕሮቴስታንት ኢትዮጵያ የመጣው በመርከብና በአውሮፕላን ተጭኖ በአውሮጳውያን ነው። አውሮጳ ደግሞ የሞሶሊኒና የሂትለር ዓለም መሆኑን ፈጽሞ አንርሳ። ከኩርንችት የበለስ ፍሬ ፈጽሞ አይጠበቅም። እንዲሁም ከባሕርዛፍ ላይ የኮክ ፍሬ እንደማይለቀም ሁሉ ነው። ማስተዋሉንና አእምሮውን ይስልብን። አገራችንን ከወረራ፥ ሃይማኖታችንን ከመከራ፥ ለማዳን ሁላችንም በአንድ ላይ

ዘብ እንቁም። ይህ የሁላችንም ሃይማኖታዊና ብሔራዊ የውዴታ ግዴታችን ነው። ይህን ባናደርግ ታሪክ ራሷን የመድገም ግዴታዋ ነውና በኤይድሱ በወባውና በሌሎችም ወረርሽኞች የምንጠፋው ጠፍተን የተረፍነውን የሰማይ ቅዳጅ በሚያህል መርከብ አሳፍረው ከፈለጉን ለስኳር ተክላ ያለቧለዚያም ለአትላንቲኩ ውቅያኖስ አሣንበሬ የተራበ መጋቢ ናቸውና ወስደው ይሠጡናል። ከዚያ በኋላ ገነት በምድርን ኢትዮጵያን ለእነሱ መኖሪያ ብቻ ያደርጓታል። እንዲያውም አንድ ማስረጃ ላቅርብ። እንዲህ ይላል። «Ethiopia is a paradise for white people» [ኢትዮጵያ ለነጮች መኖሪያ ምድረ ገነት ናት] Baron Roman Prochazka የተሰኘ ጸሓፊ *Abyssinia the Powder Barrel*, ገጽ 16 በተሰኘው መጽሐፉ ላይ ኢትዮጵያ ቀደም ተብላ የነጮች መኖሪያነት የተመደበችና የመወሰድ ተራዋን የምትጠብቅ መሆኗን ልብ ይሏል። እኛም ወይንም ዘሮቻችን ነበሩ ይባላል ወደሚለው የታሪክ ተረት ይሸጋገራሉ። ይህን እውነታ በአፍሪቃውያን አሜሪካውያን ወገኖቻችን ሕይወት የምንማረውና እየተማርን ያለነው እውነታ ነው። ለዚህ ሁሉ የግፍ አገዛዝና ቀንበር የጀመሩት በኢየሱስ ስምና ባነገቱት መጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ነው።

አባቶቻችን ጠንካሮች አዋቂዎችና አስተዋዮች በመሆናቸው ሕይወታቸውን ለአገራቸውና ለሃይማኖታቸው ሠውተው እስከዚህ አድርሰዋል። ይህ ትውልድ ደግሞ ምንም ያለውን ነገር ሁሉ ቢነጠቅም ቅሉ ለመኖር ያህል አለ። ይሁን እንጂ የማንነቱ መታወቂያ፥ የዜግነቱ መለያ የሆነው መሬቱን ሳይቀር ተነጥቋል። የቀረችው ይችው ሃይማኖቱ ነበረች እርሷንም ዙሪያዋን ከበው እየቦጫጨቋት ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ የሃይማኖት ነፃነት አለ በሚል ሽፋን ኢትዮጵያ ያልገባ የሃይማኖት ድርጅት የለም። ሥጋቴ ግን ነገ ከነገ ወዲያ የሰው መሥዋዕት የሚያቀርብ ሃይማኖት ገብቶ ልጆቻችንን እያረደ እንዳይጨርስብን ነው። በኢትዮጵያ የማይሠራና የማይፈፀም ግፍ እንደሌለ ደግሞ የምናውቀው ነው። እሱ ያመጣውን መከራ ራሱ እስከሚመልሰው ድረስ በትዕግሥት ማየትና መጠበቅ ነው የሚለው የማደናገሪያ አስተሳሰብ ከአእምሯችን ታጥቦ መውጣት አለበት። ሃይማኖት አንዲት ናት። የያዝናት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በሚገባ የምታጸድቅ ናት። ሃይማኖታችሁን አትለውጡ። ብትለውጡ ትገባላችሁና ወደ ድጡ ወደ ማጡ ከማንነታችሁ በምንም ዓይነት አትገላበጡ።



ይልቁንስ አሁን የመንግሥት አስተዳደር፥ የትምህርቱ ሥርዓት፥ ወደ ኢትዮጵያዊነት ይለወጥ ቢባል የተመቸ ይሆናል። ያለበለዚያ ግን ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ወደ ጴንጤነት መለወጥ ማለት ዕጅንና እግርን በስለት መቆራረጥ ነው። ኧረ! ለመሆኑ የሃይማኖት እጦት ነው ችግራችን? ይህማ ይህ ራሱ በደዌ ላይ ደዌ፥ በበደል ላይ በደል የቆሰለውን ገላችንን በገል መፈቅፈቅ ነው። ታዲያ ሕመሙን የሚያውቀውና የሚሰማው ባለ ቁስሉ እንጂ ለፈገፋጊውማ ጨዋታና ፌዝ ነው። እንግዲህ የደበሎው ወይንም የዳባው ማራገፍ ምንን ለማደናገር እንደሆነ እናውቀዋለን። ጀርባችንን በስለት ለመውጋት ሲፈልጉ ኋላ ኋላችንን ይሄዳሉ። ለምን ሲባል ቀዳሚ ናችሁ ለትሕትና ነው ይሉናል። ለሚያደርጉት ሁሉ ምክንያት አላቸው።

ነገር ግን ዓላማቸው የያዙትን ጩቤ ከጀርባችን ለመጨመር ነው። አሁንም ችግራችን ሃይማኖት አይደለም። ችግራችን እናንተን መልምሎ ከመካከላችን መሠንቀሩ ላይ ነው። የናንተ መኖር መንገዳችንን፥ በራችንን የተሰበረ ጠርሙስ መጣያ ማድረጉ ላይ ነው። ከዚያ በተረፈ እንኳን የናንተ ሃይማኖት ኢየሱስን ሊያስተዋውቀን ይቅርና የሚያጣላንና የሚያራርቀን ነው። ይሁንና ባጭሩ የምንለው፥ እንደ ፀሐይ የሚሞቅ፥ እንደ ሻሽ የሚያደምቅ ሃይማኖት አለን። ስለዚህ ማርን ሸጦ ምን ይገዟል ነውና ስለ ኢየሱስ ብላችሁ ተዉን። የሰላማችንን ምንጭ አታደፍርሱብን። እኛን ከውስጥ የፈጥኝ አሥራችሁ ቤታችንን በላያችን ላይ ዘግታችሁ በእሳት እያቃጠላችሁብን ነው። ኢትዮጵያዊነታችን እስከ ማንነታችን ድረስ ያለምንም ቅሪት እንዲነድ እያደረጋችሁ ነው።

የምዕመናን ድርሻ ምንጊዜም የነበረና ያለም ነው። አሁን ግን ያለው የሠበካ ጉባዔ ቤተ ክርስቲያንን ለማስተዳደር በቃለ ዓዋዲ አዋጅ ቁጥር ሕጋዊ ሥልጣን ያለው ሆኖ የመክሰስና የመከሰስም መብቶች አሉት። በእኒህ ግዴታዎችም መሠረት እንደ ውስጠ ደንቡ መሠረት ከተወሰነ ዓመት አገልግሎት በኋላ በምዕመናን ምርጫ ሹመትና ሽረት ሳይሆን ያላገለገለው ያገለገለውን በመተካት ሸክም ማቃለል ነው። የሠበካ ጉባዔ አባልነት ነፃ ሃይማኖታዊ አገልግሎት እንጂ ደሞዝ የሚከፈልበትና የሚሠሬበት አይደለም። ይሁን እንጂ የሠበካ ጉባዔው ቀጥሮ የሚያሠራቸው ባለሙያዎች አሉት። በኢትዮጵያ ውስጥ የሠበካ ጉባዔውን በበላይነት የሚመራው የደብሩ አስተዳዳሪ/አለቃው ሲሆን የቀረውን በምዕመናን ይያዛል። ነገር ግን በውጭ አገር ግን የሠበካ ጉባዔ አመሠራረት በቃለ ዓዋዲው መንፈስ ይሁን እንጂ የሥልጣኑን ዳር ድንበር ራሳቸው ተመራጮች ምዕመናን ብቻ ሆነው ይገኛሉ። ካህኑ ግን ደሞዝተኛ ማለት ተቀጣሪ እንጂ

ምንም ዓይነት ሥልጣን ፈጽሞ የለውም። ለሠበካው ጉባዔ ምቹ ካልሆነም የማሰናበቻ ደብዳቤ ይጻፍለታል። በቀባል ቋንቋ ይባረራል። ይህንንም እንደሚከተለው በአጭሩ እንመለከታለን።

በውጭ አገር ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የሠበካ ጉባዔዎችና ምዕመናን ይዘትን በንመለከተው እብዛኛው ከአገሩ ውጭ የሚኖረው ሕዝብ በሦስት ምክንያቶች ከአገሩ የወጣ ነው። የመጀመሪያዎቹ አወጣጥና አመጣጥ ለከፍተኛ ትምህርት መጥተው ከዚሁ የቀሩ ናቸው። በሁለተኛና በብዛት ያለው/ከፍል ግን ከዘመነ ደርግ ጀምሮ በስደት የመጣው ነው። አሁን ደግሞ ከአምስትና ከሰባት ዓመት በፊት ደግሞ በሎተሪ የመጣውና የሚመጣው ነው። ታዲያ በእኒህ በሦስቱ ምክንያቶች የሚመጣው ሕዝብ ቁጥሩ እየጨመረ መጥቷል። በዚያውም ላይ መባዛትም ቀጥሏል። ይሁን እንጂ ይህን በየቦታው የሚገኝ ኢትዮጵያዊ በአንድ አቅጣጫ ለመምራት የማይቻሉባቸው ምክንያቶች አሉት። ያም ሆኖ ልዩነቱን አቻችሎ ሁሉም ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል አስተዋጽኦም ያደርጋል። ክርስትና ያስነሣል። ለወላጆቹ ፍትሐት ያስፈታል ተዝካርም ያወጣል። ዓመታዊ የአባልነት ክፍያም ያደርጋል። ይህ ሁሉ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኗ ቀድማ ደርሳ ቡራኬ የምሠጥህ እኔው ነኝ ብላ የበላይነቱን አልወሰደችም። ይህም በመሆኑ በልዩ ልዩ ምክንያት የሚገናኙና የሚተዋወቁ ግለሰቦች በመሰብሰብ ቤት ተከራይተው ካህን ቀጥረው አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ።

እኒህ ሰዎች የጋራ የሆነ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው ወይንም ካንድ አካባቢ የመጡትን አሰባስበው የመንደር ልጆች ቤተ ክርስቲያን ያቋቁማሉ። ይህም ኢትዮጵያዊነቱንና ሃይማኖታዊውን አፈፃፀም ያስለውጠዋል። ይህም ሁኔታ አሁን ለተፈጠረው ችግር መጋቢ ነው። በዚህም ምክንያት የሠበካ ጉባዔ አባላት በሚፈጥሩት ያለመግባባት ለሁለትና ለሦስት የተከፈሉ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። በገንዘቡም ላይ ክስና ክርክር በየፍርድ ቤቱ ሲዋቀሱ ይታያሉ። ቤተ ክርስቲያኗ ከእንዲህ ዓይነቱ ዕይታ ውስጥ ሆና ትገኛለች። ይህ በእንዲህ እንዳለም አሁን በአሜሪካ የተከሠተው ሁኔታ ለካህናት ብቻ ሳይሆን ጳጳሳትም የፖለቲካ ጥገኝነት በመጠየቅ መምጣት ጀመሩ። አሁን ነገር ተበላሸ። ጳጳሳቱም ምዕመናኑም ሁሉም ስደተኛ ሲሆኑ የስደት መንግሥት ማቋቋም ተሞከረ በቤተ ክርስቲያን በኩል ተቻለ። ቤተ ክርስቲያኗ የአባብ ጉዳንድ መለኪያ ዕጅ ሆነች። በዚህም ምክንያት የአሜሪካው ሲኖዶስ ያውም «ሕጋዊው ሲኖዶስ» ተብሎ ተሠየመ። ታቦቱ ጃንጥላው ቃጭሉ ክበሮውና ጸናጽሉ ሁሉም መጡ። ጳጳሱም ባርከ ምሥራቀ ወምዕራበ



ሰሜነ ወደቡበ መሥዕ ወዓዜብ ሊባ ወባሕር ብለው ባረኩ። ታቦት ወጣ መዘምራን በከበሮ አደመቁት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነን ግን ኢትዮጵያ ካለው ሲኖዶስ አስተዳድር ጋር ግን አይደለንም እየተባለ ከስብከተ ወንጌሉ ጋር በማሰረጊያነት መነገሩ ቀጠለ። ምዕመናኑ ታቦት ከወጣላቸው ከበሮ ከተመታላቸው ቅዳሴው ከተቀደሰላቸው ከዚያ ውጭ ያለውን ጣጣ መስማትም ማወቅም አልፈለጉ። ቢጠይቁም መልስ የሚሰጣቸው የለም። ሁሉም በተአቅቦ ውስጡን ሳያባዩ አብያተ ክርስቲያናት በዙ ተባዙ። የደረሰ ሁሉ የሚቀድስባቸው መስቀል ያለው ሁሉ የሚባርክባቸው ሆኑ። እናት ቤተ ክርስቲያንን በመጎናጸፊያ ጠቅለው አስቀመጧት። የጳጳሳቱም ቁጥር እያደር በረከተ። በጋራ አንድ ላይ ሆነን የሲኖዶስ መንግሥት እንመሥርት ብለው ተነሡ። ከጥቂት ጊዚያት በኋላ ተለያዩ። ከእናት ቤተ ክርስቲያንና እንደገና በአሜሪካ ልዩነት ተፈጠረ። ይህ መከር ለፀረ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠላ በረከት ዝናመ ምሕረት ሆነላቸው። በዚህን ጊዜ ነው የቃጭል የካህንና የከበሮ ጉዞ ወደ አሜሪካ መጉረፍ የጀመረው። በሠበካ ጉባዔ ስም የፖለቲካ ድርጅቶች መቆጣጠሩን ያዙት። ጳጳሳት ሳይቀሩ የጸሎታቸውን ቅላጼ ቀየሩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ አሜሪካ መጥቷል። ይህ ነው ሕጋዊው ብለው የቀድሞውን ፓትርያርክ ከኬንያ አስመጡ። አሁን ከደረሰበት ደረጃ ደርሷል። ኤጲስ ቆጶሳት ተሹመዋል። አባል አብያተ ክርስቲያናት አይዟችሁ እየተባሉ ነው። በዚህም ምክንያት በተለይ በአሜሪካና በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሦስት ተከፍላለች። የማይሠራ ነገር የለም። ቢኖር ከጸሎቱ መልስ እርስ በርስ መወነጃጀል ነው። መቼም እድሜ የማይለመንበት ዘመን ነው። ይሁንና አንደኛ የእናት አብያተ ክርስቲያናት ሁለተኛ የአሜሪካው ሲኖዶስ ሥር የሚገኙትና ሦስተኛ ከሁሉም ያልሆኑ ገለልተኞች ናቸው። በዚህ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያኗ አንድነትና ሦስትነት አግኝታለች።

ማዕድናቱም እንደዚሁ ነው። የኢትዮጵያ ዓልማዝ ልዩና ታዋቂ እንደነበር የምንረዳው በጥንቱ ዘመን በአንደኛነት ታዋቂ የነበረው የኢትዮጵያ እንቁ በተለየ ስሙም እንቈጳዝዮን ነበር። ከገናናነቱ የተነሣ ይህንኑ ምርጥ የክብር ድንጋይ በመጽሐፈ ኢዮብ ላይ ተወስቶ እናገኘዋለን። እሱም የጥበብ ማነፃፀሪያና ማወዳደሪያ ሆኖ ነው። እንዲህ ይላል። «የኢትዮጵያ ቶጳዝዮን አይተካከላትም» [ኢዮብ፣ 28:19] ስለዚህ ግዕዝ ያልመዘገበው ጥበብ ፍልስፍና ታሪክ መድኃኒት ቅመራ ምሕንድስና የለም። የዓለም ጥበብ ምንጭ ነው።

ነገር ግን በዚህ መታወቅ ቀርቶ በተረት እንኳ የሚናገርልን የለም። ግዕዝ ከትምህርት ቤት እንዳይሠጥ ቀደም ብሎ ዘመናዊው ት/ቤት ሲጀመር ማዕቀብ ተደረገበትና ነው። ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ግዕዝ ሲባል ለቅዳሴ ለማኅሌትና ለፍትሐት ብቻ አገልግሎት መስጫ አድርገው ይመለከቱታል። እንዲያውም ከሕዝቡም አመክሮ እንደምንረዳው በኔ ሞት አፈር ስሆን ሃሌ ሲሉብኝ ከመባል ደርሷል። ቤተ ክርስቲያን ከቤተ መቅደሱ ጀምራ የትምህርት ሚኒስቴር ሆና በመኖሯ ብቻ ስትገለፃልበት ትታያለች እንጂ ግዕዝ የሁሉም ነው። የጥበብ የምርምር የሕክምና የምሕድስናና የቅመራ ማለት የስሌት ሁሉ ቋንቋ ነው። ወጣቶች አጥኑት። ትምህርት ቤት በሩ ተከፍቶለት እስከሚጠና ድረስ ያላችሁን ወርቃማ የወጣትነት እድሜ ግዕዝ ሳታጠኑበት እንዳያልፍ እማፀናችኋለሁ። የሚፈለገውን ሁሉ ታገኙበታላችሁ። የዓለም ጥበብ ምንጩ ከዚሁ ቋንቋና መጻሕፍት እንደሚገኝ ላስገነዝባችሁ እወዳለሁ አደራም እላለሁ። ግዕዝ ማጥናት ለእናንተ ከባድ አይደለም ቆሎ እንደመቆርጠም ነው። ቀላል ነው። ካንድ ዓመት በላይ አይወስድባችሁም። ጥቅሙ ግን እጅግ በጣም ታላቅና ብዙም ነው።

ዛሬ አፍሪቃ በምዕራባውያን አድማና ሴራ ተበጣጥሳ ባሕሏንና ቋንቋዋን አጥታ የነጣችበትና የገረጣችበት ጊዜ እንደሆነ ታውቃላችሁ። በየትም የአፍሪቃ አገር የሚናገሩበት ቋንቋ የቅኝ ገዥዎቻቸው ቋንቋዎች ናቸው። ይህን ጉዳይ ወደራሳችን መለስ ብለን ስናየው በወላጆቻችን እንዴት እንኰራለን። እንዴትስ እንከብራለን። በእነሱ ደም በእነሱ አጥንት እኛ በማንነታችን ላይ እንገኛለን። በራሳችን ፊደል እንጽፋለን በራሳችን ቋንቋ እንናገራለን። ይህን ጠብቀው ያቆዩን ወላጆቻችንን እናከብራለን እናመሠግናለን። እኛም ይህን አደራ ጠብቀን ለልጆቻችንና ለልጅ ልጆቻችን ማስተላለፍ ታሪካዊ አደራ አለብን። የማንረሳው ግን ቋንቋችንና ፊደላችንን ወደ እነሱ ለመለወጥ የሚያደርጉትን ሤራ አተኩረን እንመልከተው። ከኛ ተበድረው መልሰው ሊያበድሩን አይገባም።



በጽኑ ልንዋጋው የሚገባ ጉዳይ ነው። ሌሎች የአፍሪቃ አገሮች ምን ያህል እንደሚኰሩብንና እንደሚመኩብን አንዘንጋ። ዛሬ የአፍሪቃ አገሮች የሚናገሩበት ቋንቋ ልዩ ነው። የባዳ ነው። ከዚህ ለመውጣት በትግል ላይ ናቸው። የስዋሂሊኛ ቋንቋ መጠናት ራሱ አንዱና ትልቁ ምሳሌ ነው። ስዋሂሊኛን በግዕዝ ፊደል ሲጽፉ ነው ምሉእ የአፍሪቃ ቋንቋ የሚሆነው። ይህን ደግሞ ነገና ከነገ ወዲያ ይሆናል። ከዚያ ደግሞ ግዕዝ የአፍሪቃ ልሣንነቱን ያረጋግጣል። የግንዛቤ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ ለአፍሪቃ ነፃነት ተዋግታለች ረድታለች አበረታታለች። የአፍሪቃ አንድነት እንዲመሠረትም እጅግ ታላቅ መሥዋዕት ከፍላለች። ለዚህም ነው የአፍሪቃ አንድነት ዋና ከተማ እንድትሆን የተመረጠችው። ይህ ቀላል ምርጫ እንዳይመስለን በክብር ልንቀበለውና ልናከብረው ይገባል። በዚህ ዕድል በዋና ከተማነታችን ብዙ የምንመግባቸው ብዙ የምንሠጣቸው አሉን። ከክትፎውና ከጠጁ ባሻገር ማለቴ ነው። የአፍሪቃ ቋንቋ ግዕዝ ነው አጥኑት ብለን ለመቀለቀል በመጀመሪያ ራሳችን ከት/ቤት እንዲገባ ስንፈቅድ ነው። ይህን ብናደርግ ታሪክ ሲያወድሰን ይኖራል። ላለውና ለመጭው ትውልድም ብሔራዊ ቅርስ እንተውላቸዋለን።

የሚገርመው ግን አፍሪቃውያን ምንም እንኳ በላያቸው ላይ ያለውን የምዕራባውያን ተጽእኖ ሁሉ ተቋቁመው ወደ ማንነታቸው ለመምጣት የማያደርጉት ነገር የለም። ሆኖም ገና ናቸው። የወደፊቱ ትውልድ ግን ይችላል። በርግጥ ይችላል። ጨርሶ ነፃ ይወጣል። የዛሬው የአፍሪቃ ነፃነት ሰንደቅ ዓላማ ከማውለብለብና የራስን ሰው መሪ አድርጎ ከመመልከት በስተቀር ገና ፍፁም ነፃነት አልተጨበጠም። ገና በዓየር ላይ ነው። በእያንዳንዳቸው በአፍሪቃ መሪዎች ላይ ያለው ተጽእኖ በቋንቋ የሚገልጹት አይደለም። እንዲያው ለመኖር ሲባል የሚደረግ መፍጨርጨር ነው። ይሁንና ይህን የአፍሪቃን ችግር የመዘዝሁበት ምክንያት አለኝ። እሱም በአፍሪቃ ውስጥ ሁሉም ዓይኑን ከፍቶ የሚመለከታት አገር የአፍሪቃ አንድነት ዋና ከተማ የሆነችው ኢትዮጵያ ለአፍሪቃ አንድነት የምታገለግለው በብዙ ዘርፍ ነው። ከዋና ከተማነት አልፋ ተርፋ ፊደሏን ቋንቋዋን አፍሪቃውያን ይፈልጉታል ሊማሩት ይሻሉ። ሊናገሩበት ይወዳሉ። ታዲያ ለዛሬው ወጣት ግዕዝን ማጥናት ለነገው የአፍሪቃ ትውልድ ቋንቋ አስተማሪ ለመሆን ዕጩነት ነው። ለዚህ ዓቢይ ሥራ እናንተው አይደላችሁምን? በእርግጥም ናችሁ። ከያላችሁበት ጀምሩት። በተለይም የግል ት/ቤቶች ከፍታችሁ ወገኖቻችሁን በዕውቀት የምትመግቡ ኢትዮጵያውያን ግዕዝ በየት/ቤቶቻችሁ እንዲሠጥ እስቲ በር ክፈቱ። ታሪክም ያወድሳችሁ። ኢትዮጵያዊነት አደራችሁንም ተወጡበት።

ዛሬ የኢትዮጵያን በተለይም ይህን ጥንታዊ ቋንቋ የዓለም ጥበብ ምንጭ የሆነውን ግዕዝን እጅግ ቁጥሩ ብዙ የሆነ በአሜሪካ በካረቢያን ደሴቶች የሚኖሩ የአፍሪቃ ተወላጆች ለመማር እጅግ በጣም አድርገው ይሻሉ ይመኛሉ። ይህን ፍላጎታቸውን የሚያሟላላቸው ማን የሚሆን ይመስላችኋል። እናንተው የቋንቋው ባለቤቶች ናችሁ። ባንድ ዓመት ትምህርት የዕድሜ ልክ ፀጋና ሀብት ማግኘት መሆኑን ልብ በሉት። አፍሪቃውያን በራሳቸው ፊደል መማርና መጻፍ የማይቆጩ ይማስላችኋል? እጅግ በጣም ነው የሚቆጩት የሚንገበገቡት። ሙላ አፍሪቃ ኢትዮጵያ ተብሎ መጠራትን እንደሚመርጡ ግንዛቤ አድርጋችሁ ታውቃላችሁን? ካላደረጋችሁ እስቲ። ዛሬ ጅቡቲ ሶማሊያና ኤርትሪያ ሱዳን ተብሎ መጠራራቱን ራሳቸው ምዕራባውያኑ የኢትዮጵያን ስም ስመጋረድ ምሥራቅ አፍሪቃ በማለት እየጠሩን ነው። የሚፈጽሙት ያለው ትንቢት ነው። እኒህ አገሮች ድሮም ምሥራቅ አፍሪቃም ኢትዮጵያም ነበሩ አሁንም በውስጣቸው በመልካቸው በቋንቋቸው በባሕላቸው አንድ ናቸው። ልዩነት የተፈጠረባቸው ነፃ መንግሥት ነፃ ሰንደቅ ዓላማ ማውለብለቡ ላይ ነው። ይህም ሲደረግ በውጭ ተጽእኖ እንጂ በሕዝቡ ፍላጎትና ምኞት እንዳልሆነ የምታውቁት አይደሰምን?

ወደ አደራዬ ወደ ተማጽኖዬ ልመለስ ግዕዝ አጥኑ። ቅኔ ቤት ሂዶ ቁራሽ ለምኖ መብላት ሳያስፈልጋችሁ መዝሙር እንደምታጠኑት ሁሉ ግዕዝንም አጥኑት። በነፍስም በሥጋም ይጠቅማችኋል። አንድ ምሥጢር ላማውታችሁ ልብ ብላችሁ አዳምጡኝ። ምዕራባውያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ሞከሩ አልቻሉም ተሸነፉ አፍረውም ተመለሱ። ይህ ያንድ ኢጣሊያን ኀፍረት ብቻ አይደለም ለመላው ቅኝ ገዢዎች በሙሉ እንጂ! ኢትዮጵያ ደግሞ ቀኝገዥዎችን በሙሉ ተዋግታ ያሸነፈች አገር ማለት ድሉ ለመላው አፍሪቃ ሕዝብ ነው። ይህን ኩራት ይህን ድል አድራጊነት ያበገኘች አገር በዓለም ላይ ብርቅ ድንቅ ሆና ታየች ተነገረች በተለይም የአፍሪቃ ዝርያ ተወላጅነት ባላቸው ሁሉ ዘንድ ነበር። ነውም። በአሜሪካ በኢትዮጵያ ስም የጥቁሮች አብያተ ክርስቲያናት መሠየም ጀመሩ የዳግማዊ ምኒሊክና የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስሞች እንደ ኮከብ ለሁሉም የሚታዩና የሚያበሩ ሆኑ። ይህን አፍሪቃ አፍሪቃ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ለማጥፋፋት ምን አድማ ተጀመረ። የኢትዮጵያን ስም ያስመጥራት በምትኩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይቀር ደቡብ ግብፅ ሱዳን ኩሽ አቢሲኒያ የሚሉትን ስሞች ማደናገሪያ አደረጓቸው። አሁን ደግሞ ምሥራቅ አፍሪቃ ወዘተ... እየተባልን ነው።



ወጣቶች ሆይ! ይህ ብቻ አይደለም ጉዱ የቤቶቻችንን ዶሮዎች በቆቅ እየለወጡብንም ነው። ዛሬ የግዕዝ ፊደል ቀዳሚ ፊደላት መሆኑ እየታወቀ ግዕዝን ወደ ላቲን መልሰው በጦርነት ያላገኙትን ምርኮ በዕጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ እያጠፉብን ነው። ኢትዮጵያውያንን መበታተን ማጠላላት በረሀብና በጉስቁልና መተብተብ ፍቅር አንድነት እንዲጠፋ ማድረግ ሰዎችን መከፋፈል። መፈንቅለ መንግሥት ማዘጋጀት ይህን በመሳሰለው የምትኀሳቆለው ማን ናት? አሁንም ቢያንስ ቢያንስ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሰባት በላይ ነፃ አውጭ ድርጅቶች አሉን። እርሻ እንዳይታረስ ትምህርት እንዳይቀጥል ዕድገት እንዳይመጣ ሕዝቡ ወደ ልማትና ወደ ሥልጣኔ እንዳይጓዝ የሚደረገውን ትንቅንቅ የምታዩትና የምትሰሙት አይደል? ኢትዮጵያን በበለጠ ብዙ አገር ለማድረግ ቢያንስ ቢያንስ አምስት አገሮችን ሠንጥቆ ለማውጣት የሚደረገውን ጥረት ታዩት የለምን? ይህ ሁሉ ለኛ ካንድ ኢትዮጵያ ይልቅ ብዙ ኢትዮጵያ የተከፋፈለች ኢትዮጵያ ለማድረግ ለጽድቅ ይመስላችኋልን? ኢትዮጵያ በፊደሏ በባሕሏ በቋንቋዋ የመላው አፍሪቃ ነፍስ መሆኗን ስለሚያውቁ ማስናከያ መፍጠር ታላቅ ሥራ ከፍተኛ በጀት የተመደበለት ሥራ ነው። ይህን ወጣቶች ማወቅና መገንዘብ አለባችሁ። ይህም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተረሣና እየተዘነጋ ሲሄድ እነሱ በዕቅዳቸው እያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት ወይንም ክፍለ ሀገር ሌላ መንግሥት ነፃ አገር ሆኖ የእነሱ የዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ለጊዜው ለዘለቄታው ደግሞ በሽቦ አጥረው በዘበኛ አስጠብቀው ለመኖር ነው። ታዲያ ወጣቱ ሆይ! በገዛ አገርህ የፈረንጅ በር ጠባቂ ሆነህ ለመኖር መቼም ቢሆን አትመኝም። ነገር ግን መንገድ ከጠፋ ውርደት ከመጣ ደግሞ ምርጫ የለህም። ዛሬ ግን ምርጫ አለህ። በቅድሚያ የራስህን ማንነት አጠናክረህ ያዝ። እንደ ጥሩ ምሳሌም የሚሆነው ዛሬ መዝሙርህ በየመኖሪያ ቤቱ በየአውቶቡሱ በየቡና ቤቱ በየጠጅ ቤቱ በየመንገዱ ከቤተ ክርስቲያን እንኳ ሞልቶ ተርፎ ስታዩት ሕዝቡ ከእናንተ ጋር መሆኑን መረዳት አይቸግራችሁም። ነገ ከነገ ወዲያ ደግሞ ግዕዙ ሲጠና ግዕዙ ሲታወቅ መጻሕፍቱን ስትመረምሩ ምሥጢሩን ስታውቁት እጅግ ትደሰታላችሁ። ተፈላጊነታችሁም በሠፊው ይጨምራል ይወደዳል ይፈለጋል። ታዲያ ጊዜ አይባክን ነገ ዛሬ አይባል አሁኑኑ ትምህርቱ ይጀመር።

ይህን ስታደርጉ በግዕዝ ፊደላት መጻፉን አስትተው በሮማን ያውም ዘሮቻችንን በመርዝ ጨስ በጨረሱት በጠላቶቻችን ፊደል የሚጽፉትን ወገኖቻችንን ዕጅ ወደ ኋላ እንዲሰበሰብ እናደርጋለን። ይህን ሲያደርጉ በቅንነት በጥናት በእውነት ከግዕዝ ፊደል ይልቅ የሮማን ፊደል ምቹ ሆኖ ይመስላችኋል? አይደለም አይሆንምም። ግን

ስዚሁ ሆን ተብሎ የሠለጡኑ እነሱ ደግሞ ያራቡት ከጥላቻ ጋር ጥላቻው ደግሞ ከግዕዝ ፊደል ጋር ነው። የቅኝ ገዥዎች ቋንቋ ተብሎኮ ተሠይሟል። እጅግ የሚያሳዝን ነው። የሮማን ፊደል ከግዕዝ መቀዳቱን ቢያውቁ ኖሮ ቢያጠኑት ኖሮ እንዴት በደነቃቸው በነበር? እንዴትስ በገረማቸው? በአገራችን ሙጀሌ የምትባል ቁንጫ አለች። በእግር ገብታ አግርን የምትበላ። ይች ትንሽ ቁንጫ በጊዜው ተከታትለው ካልነቀሏት እግርፅ በመጥረቢያ ቆርጠው የጣሉትን ያህል ሙልጭ አድርጋ ትቆራርጣለች። በሙጀሌ የተበሉ ሰዎችን እግር ስታዩ ትገረማላችሁ. አካሄዳቸውንም ጎታታና ጠማማ አድርጋባቸዋለች። በቶሎው በጊዜው እርማት ካልተደረገበት ካንዱ ትውልድ እንደምንም ብሎ ወደ ሌላው ከተሸጋገረ መልሶ ለማስተካከል በጣም አስቸጋሪና አደገኛ ይሆናል። በሽታው ከዋለ ካደረ መድኃኒት ካላገኘ የማይገድለው ይገድላል። ስለዚህ አስፈላጊው ርምጃ አሁንኑ ቢወሰድ መልካም ይሆናል።

ከዚህ ላይ አብሬ አደራ የምለው በያላችሁባቸው አብያተ ክርስቲያናት ያሉ የሰበካ ጉባዔዎች የግዕዝ መምህራንን ሊያገኙላችሁ ይገባልና ማሳሰቢያው ይድረሳቸው። በተለይማ የየህገረ ስብከቱ ጽ/ቤቶች ከዚህ የበለጠ ምንስ ታላቅ ቁምነገር አላቸው? ይህንስ ከማድረግ ምንስ የሚገታቸው አለ? ለነገሩማ ሥልጣነ ክህነት ከመቀበል በፊት ግዕዝ መማርና ማወቅ የግዴታ ግዴታ ማዕቀብ መጣል አለበት። ተጽእኖ መደረግም ይኖርበታል። ይህን የመሰለውን ውሳኔ ደግሞ የሚወስደው ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲገነዘበው በእናንተ በወጣቶች በታዳጊዎች ስም በታላቅ ጩኸት እጠይቃለሁ። ሥራው ግን የእነሱ ነበር። ሆኖም ምሳ ደርሷል ማዕድ ቀርቧል ተብሎ እንደሚነገረው እናስታውሳቸው። ይሁን እንጂ እያንዳንዱ የህገረ ስብከት ጽ/ቤት ሊያደርገው የሚችለው ዓቢይና ቀዳሚ ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ በግዝትም እንኳ መደረግ ያለበት ሥራ ነው። ግዝቱም ከዚህ ላይ ቢያርፍ ይሠራል። የቀደሙ አባቶች የደነገጉት ሕግም አለ። እሱም ልጁን የማያስተምር ወላጅ የገንዘብ ቅጣት እንዲደረግበትና እንዲገዘት ይወስናል። ይህም በዓፄ ምኒልክ፥ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥታት ሁሉ ተፈጽሟል። በደርግም ጊዜ መሠረተ ትምህርት «ያልተማረ ይማር የተማረ ያስተምር» ተብሎ ዘመቻ ተደርጎበታል።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ትምህርት ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳል። የወጣቶች የግዕዝ መማርና ማወቅማ ታሪካዊ ብሔራዊና ሃይማኖታዊም ነው። እንዲሁ ከሩቅ ሲመለከቱት ነገሩ ቀላል ይመስላል እንጂ አይደለም። ይህን ማድረግ እጅግ በጣም ጠቃሚ



ነው። ከመሬት ውስጥ ወርቅን፥ ዓልማዝንና ዕንቊን ቆፍሮ የሚያስወጣ ቋንቋ ነው። ግዕዝን አውቆ መገኘት ማለት ነዳጅን ቆፍሮ የማውጣት ያህል ያስቆጥራል። በምኞት ብቻ ሳይሆን በተግባር ተተርጉሞ ሲገኝ ብቻ ነው እውነተኛ ሀብትና ፀጋ መሆኑን መረዳት የሚቻለው። ወጣቶች ብረት ለብረት ሲጋጭ ስለት እንደሚወጣው ሁሉ እርስ በርሳችሁ ተማማሩ። መጻሕፍት አሉላችሁ። ባይሆን የሰበካ ጉባዔያችሁ መጻሕፍትን ይግዙ ወይንም ትያትር አዘጋጅታችሁ ገንዘብ አግኝታችሁ የግዕዝ መማሪያ መጻሕፍትን ግዙ። ከጀመራችሁት በጎ ሥራ ማድረግ ደስ የሚላቸው ግለሰቦችና ድርጅቶችም ይተባበሯችኋል። ጊዜ አይሠጠው በቶሎው ጀምሩት። እስካሁን በከንቱ የጠፋውና የባከነው ጊዜ ይበቃል።

ወጣቶች ሆይ! የግዕዝ ትምህርት እንዲሁ በሩቁ የሚያዩት ጉዳይ አይደለም። ከፍ ብዬ እንደ ጠቀስኩት ሁሉ ብርቅ ድንቅ ነው። ግዕዝ እንደ ስሙ ትርጓሜ መጀመሪያ የሰው ልጅ አፍ መፍቻ ቋንቋ ነው። ምዕራባውያን ታሪክ ፀሓፊዎች እንደሚያወሩት በየመን በኩል የመጡት ሰዎች የሚናገሩት የነበረ የዐረብኛና የዕብራይስጥ ወገን ነው እንደሚሉት አይደለም። የእኒህ ቋንቋዎች አባትና እናት እንጂ! ለዚህ ሁሉ ማስረጃው ግዕዝ የመጀመሪያ ቋንቋ ለመሆኑ እንዲህ ሲል ተጽፏል። «ወአሐዱ ነገሩ ለኩሉ ዓለም ወአሐዱ ቃሉ። [ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች።] ዘፍ. 11:1 ሲል ይገኛል። ይህን ቃል በጥሞና መመልከት ነው። ግዕዝ ይህን ያህል የመጀመሪያ ቋንቋ ነበር ስንል እንዲያው ኢትዮጵያን ከፍ ከፍ ለማድረግ ነውን? አይደለም እውነት ስለሆነ ነው እንጂ! ብዙ ማስረጃዎች አሉን።

ሌላ ምሳሌ ላቅርብ። የሰው ልጅ አባትም እናትም ሆኖ የተፈጠረው የመጀመሪያው የሰው ልጆች ሁሉ አባት አዳም የስሙ ትክክለኛ ትርጉም ያለው በግዕዝ ብቻ ነው። አዳም ማለት በግዕዝ አጠራሩ እድ ወእም የሁለቱ ቃላት ጥማሬ ነው። እድ ማለት ወንድ እም ማለት ደግሞ እናት ወይንም ሴት ማለት ነው። ሲነበብ ወን አጣማሪውን ቃል ትቶ አዳም ይለዋል። ይህም ቃል ወንድና ሴት ማለት ነው ብለናል። የትርጉሙን ማስረጃ እንመልከት። እንዲህ የሚል ቃል እናነባለን። «ወነደቃ እግዚአብሔር ለይእቲ ዐፅመ ገቦ እንተ ነሥአ እምአዳም ወረሰያ ብእሲተ ወአምጽአ ኀበ አዳም። ወይቤ አዳም ሶቤሃ ዛቲ ዐፅም እምዐፅምየ ወሥጋ እምሥጋየ ለትኩነኒ ብእሲትየ እስመ እምታ ወጽአት ይእቲ» [እግዚአብሔርም ይህችን ከአዳም ጎን የነሣትን ዓጥንት ቀረፀላት ሴት አደረጋት ወደ አዳምም አመጣት። ያን ጊዜም አዳም ይህች ከዓጥንቴ ዓጥንት

ድርጊት ማንበቡ ራሱ ማንነታችንን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ለክርስትና እምነታችን ምክንያት ይህ ብቻ ይበቃናል ለማለት እንጂ! እናንት ኢትዮጵያን ሃይማኖት እናስተምራለን የምትሉ የበግ ለምድ ለባሾች አርፋችሁ ተቀመጡ። እግዚአብሔር ከምታደርጉት ማደናገሪያና አሳሳች ሥራ ያውጣችሁ። ያድናችሁ። ልብም ይፍጠርላችሁ። ይህ ስለ እናንተ ያለንና የምናደርገው ጸሎታችን ነው። አሁን ስለምታደርጉት ሚሲዮናዊ ሥራችሁ ትንቢትም ተነግሮባችኋል። ትንቢቱም እንዲህ ይላል። «እግዚኦ ቦኡ አሕዛብ ውስተ ርስትከ ወአርኮሱ ጽርሐ መቅደስከ።» [ጌታ ሆይ የቀድሞዎቹ አሕዛብ ያሁኖቹ ጴንጤ መጤዎች የክብርህ መግለጫ የስምህ ማወደሻ የክብርህ ማሞገሻ ወደ ሆነችው ወደ ልዩ ርስትህ ኢትዮጵያ ገቡ። ሦስት መቶ ስድሳ አምስት ቀን ስምህ የሚቀደስበትንና የሚሠለስበትን ሥጋህ የሚፈተትበትን ደምህ የሚቀዳበትን መቅደስህንም አረከሱ። መዝ.78:1] (የትርጉሙ ማብራሪያ የራሴ ነው።)

ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሆይ! መቼም በአገርና በዓይን ቀልድ የለምና እውነቱን ተናግሮ በመሸበት ማደር የአበው አመክሮ ነው። ይህን እንድናደርግ ደግሞ የዕድሜውም የአመክሮውም የእምነቱም ሁሉ ተደማምረው ያስገድዳሉ። ዝም ብሎ ማለፍ ሳይመበክሩ መሄድ የተሰጠንን መክሊት እንደ መቅበር ነው። ይህ ደግሞ በመጭው ትውልድ ዘንድ ያስወቅሳል ያስከስሳል። ሃይማኖታዊው ትምህርትም የሚያረጋግጠው የት ነበርህ? ምን ሠራህ? የሚሉት ጥያቄዎች ከዓፀደ ሥጋ ይልቅ በዓፀደ ነፍስ የማይቀሩ መጠይቃን እንደሆኑ ተምረናል። የዚህን ዓለም ሕይወት ከአሜሪካ ኢትዮጵያ በማለት ብናሳልፈው እንኳ በኋላ ወደማይሽኮለኮሉበት ቦታ ሲሄድ መልሱ ምን ይሆናል? ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ከዚህ ላይ መሆኑን አጠንክሮ ያረጋግጣል። ስለሆነም እውነት የሚናገሩበት ቦታ ከዚህ ነው። ሳይናገሩ ከቀሩ ዋጋው ሽልማት ሳይሆን ውርደት ይሆናል። ስለዚህ እውነት መመስከሩ የውዴታ ግዴታ ሳይሆን የግዴታ ግዴታ ነው።

## ምን ይደረግ?

ሁላችንም እንደምንረዳውና እንደምናውቀው የጥበብ የቋንቋ የበው ልጅም መጀመሪያና መኖሪያ ቦታ አድርጎ የፈጠራት ኢትዮጵያ ከአምላኳ ጋር በሩቅ ሳይሆን በቅርብ የምትተዋወቅና የምትነጋገር አገር ነበረች። ኢትዮጵያውያን አባቶች የጥበብ ሰዎች ነበሩ። ታላቁ መጽሐፍ ሳይቀር የሚጠራቸው የጥበብ ሰዎች ብሎ ነው። የእነ ሆሜርንና የሄሮዶቶስን ምስክርነት ሳይጨመር ለማለት



ነው። ያሁኑ ጥበብ የተቀዳው ከእኒያ የጥበብ ሰዎች አገር ኢትዮጵያ እንደሆነ ልብ እንበል። ኢትዮጵያውያን በደመና ተጭነው ከቦታ ቦታ ይመላለሱ ነበር። በባሕር ላይም መርከቦችን ያንሳፍፉም ነበር። ይህንም ጥበብ የዛሬው በሰማይ ላይ ጉዞን፥ በባሕር ላይ መርከብንም ተክቷል። ይህ በተግባር ይታወቅ እንደነበርና ይሠራበትም እንደነበር ምስክር አለን። ለዚህም ማስረጃው ይህ ነው። «ወረበብኮ ለሰማይ ከመ ሠቅ። ዘይጠፍር በማይ ጽርሖ። ወረሰየ ደመና መከየዶ። ዘየሐውር በክንፈ ነፋስ።» በቀላል አተረጓጎም [ሰማይንም እንደ መጋረጃ የሚዘረጋ እልፍኙን በውኃ ላይ የሚሠራ ሠረገላውን ደመና የሚያደርግ በነፋስ ክንፍም የሚሄድ ይላል። መዝ. 103:2-3] ይህ አባባልና አነጋገር በአሁኑ ሰዓት በግልጽ የምናየውና የምናውቀው ነው። እሱም በባሕር ላይ እልፍኙን የሚሠራ ያለው መርከቡን ነው። በደመና የሚሄድና የነፋስም ክንፍ ያለው በቀጥታ አውሮፕላኑንና መንኮራኩሩን ነው። ይህን አስቀድመው የተናገሩትም የጥበብ ሰዎች ኢትዮጵያውያን ነበሩ። ይህን የመሰለውን በምርምር የሚገላልጡ ኢትዮጵያውያን አሁን ከየት ይምጡ? አሁን ያለው ጥበብ ሁሉ በፊት የነበረ ተግባሩም የተወደሰ ነበር።

አሁን ያለፈውን ተመልክተን ያለንበትን ሁኔታ ለናወዳድር የት ላይ ነን? ወዴትስ እያመራን ነው? ይህን የኃሳባችን መንደርደሪያ አድርገን ወደ መፍትሔ ኃሳባችን እናቅና። መፍትሔ የሌለው ነገር፥ መድኃኒት ያልተገኘለት ምች አደር የለም ብለን እናስብ። መቼም አንድ ሰው ወይንም ድርጅት ለበጎ ነገር ይነሣል መልካም ተግባራትንም ይፈፅማል። እንዲሁም በአንፃሩ ለክፉ ነገር ይነሣል የተሠራውን ያፈርሳል የነበረውን ይረሳል። ዛሬ በቤተ እምነቱ ያለውን ትርምስ ስንመለከት በእውኑ መንፈሳዊ ሥራ ነውን? በኀስ ተግባር ነው ያሰኛልን? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአብዛኛው የምትታወቀው በትምህርቷ በብሔራዊነቷ በመልካም አርዓያነቷ ነው። የቤተ ክርስቲያኒቷ አባቶችም ሥጋቸውን በድለው ለመንፈሳዊው ሥራ ያደሉ ያጋደሉ ነበሩ። ዛሬ ግን ናቸው የሚለውን ማሠሪያ አንቀጽ ደፍሮ ለመናገር ራሱ ወንጀለኛ ያሰኛል። በመንፈሳዊው ሕይወት የሥልጣን ጉጉት እንደ ሰበብ ተቆጥሮ የነበረውንና ተከብሮ የኖረውን ስሟን ማንሳቆያ አደረጉባት። ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለው ትውልድ ተነሣባት። መንፈሳዊው ሥልጣን ለመንፈሳውያን እንጂ ለዓላውያን አይደለም አይሆንምም። ቤተ ክርስቲያኗን ለማዳከም ደካማ ሰው መሾም ነው። ሠርቶ የማያሠራ ሰው ምንም ዓይነት የሥራ ፍሬ የማያሳይ ዛፍ እንኳ መቆረጥ እንዳለበት መጻሕፍት ይወተውታሉ። መንፈሳዊውን

ሕይወት ለሥጋዊው ዓለም ጋሻና መከታ ያደርጋሉ። ከውጭ ተሸንፎ ቢመጣ ሚስቱን በቁምጣ ለምን ቢባል የሚያሸንፋት እሷኑ ነውና ነው። አሁን የምናየው በተለይ የፖለቲካ ድርጅቶች ቤተ ክርስቲያንን የእባብ መግደያ ብትር አድርገው ሲጠቀሙባት ይታያሉ። ውጤቱም እባብ የገደልህበትን ብትር ወደ ገደል ወርውር ነው።

ከዚህ ላይ የግብፅን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በጥቂቱ ብንመለከት ትምህርት ይሆነናል ብዬ እገምታለሁ። ግብፅ በቅዱስ ማርቆስ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ናት። ከመጀመሪያ ምእተ ዓመት እስከ ስምንተኛው ምእተ ዓመት ድረስ ክርስትና ከዳር እስከ ዳር ተሠብኮባት የክርስቲያን አገር ነበረች። በስምንት መቶኛው ዓመተ ምሕረት ላይ ግን በአራት መቶ ሃምሳ አንድ የኬልቄዶን ጉባዔ በኋላ በክርስቶስ ባሕርይ አንድና ሁለት ምክንያት በአንድነቱ ባሕርይ ፀንታ ከካቶሊክ ከተለየች በኋላ ከእምነቱ ልዩነት ይልቅ የፖለቲካው ድጋፍና ተቃውሞ ምክንያት እርስ በርስ መጠላላት መነቃቀፍና መወጋገዝ ቀጥሎ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን ሌሎችም በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች መካከል ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ ጭቅጭቅና ክርክር ቀጥሎ በእምነትና በሥልጣን ውዝግቡ እንኳን ለእብያተ ክርስቲያናቱ ለፖለቲካው ዓለምም መበታተንን አስከተለበት።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የእስላምና ሃይማኖት ተመሥርቶ በክርስቲያኖች መካከል የነበረው ክፍፍል ለእስልምና እድገትና ሥርጭት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። በተለይ ግብፅ የሆነው በጠላትነት የፈረጇቸውን ባለ ሁለት ባሕርይ ባዮችን ክርስቲያኖች ሙስሊሞች እንዲያጠቁላቸው በመፈለግ እስልምና ግብፅ ሲደረስ በክብሮና በዕልልታ ተቀበሉት። ከዚያ በኋላ ያልሰለመ የመንግሥት ሥራ አይዝም ወደሚለው ጠባብ ሕግ ሲመጣ ምርጫው መስለምና ሥራ ማግኘት ያሊያም በረሀብ ማለቅ ብቻ ነበር። የጸኑት የግል ሥራ ጀመሩ። በእምነታቸው ጠነከሩ። የቀሩት ሰለሙ። ዛሬ ክርስቲያኖች በግብፅ እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው። ቁጥራቸውን ያሳነሠው የክርስቲያኖች እርስ በርስ መከፋፈሉ መሆኑን ልብ ይሏል።

እግዚአብሔርን ለማገልገል እስኪማ አጥልቀው ቆብ ጭነው ቅናት ታጥቀው ዓለምን ንቀው ያሉና የነበሩ አባቶች ወደ ምንኩስና ዓለም ሲገቡ ጳጳሳት እንሆናለን ቤተ ክርስቲያናችንን እንመራለን ብለው ዕቅድ አውጥተው ምንኩስናውን እንዳልጀመሩት እነሱም



ያውቁታል እኛም እንረደዋለን። ይሁንና በመንፈሳዊውም ሆነ በዘመናዊው ትምህርት አባቶች እንዲማሩና እንዲሠለጥኑ ሲደረግ አዎ በዚያን ጊዜ ለዚህ አሁን ለደረሱበት ከፍተኛ ማዕርግ ሊበቁ እንደሚችሉ ይገምታሉ እንጂ እርግጠኞች እንኳ አይደሉም። አልነበሩም። አብዛኞቹ ደግሞ በአጋጣሚ ከነበሩባቸው ገዳማት በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ዋናው ከተማ ሲገቡና ደጅ ጥናት ሲጀምሩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይነት ከዚያም የደብር አለቅነት ከዚያም እንደሁኔታውና አጋጣሚው ሁሉ ተደማምሮ ያልጠበቁትና ያልተመኙት ከፍተኛው ሥልጣነ ክህነት በራሳቸው ላይ ጠለቀላቸው። ከእግራቸው ሥር ወደቀላቸው። ቢከብዳቸውም ባይችሉትም ቅሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሾመን ማክበር ልማዱ ነውና ያልጠበቁትና ያላሰቡት ሕይወት ውስጥ ዘው ብለው ገቡ። ይህም ሢመት ያለ ድካም ያለ እንግልት ያለ ፈተና ያለ ውጣ ውረድ እንዲሁ በስጦታ በመገኘቱ የአያያዙም ሁኔታ ያን ያህል ጥንቃቄ አልተደረገለትም። የገቡትም ቃል ኪዳን እንደ ዘወትር ጸሎት እንዲሁ በቃል የሚነበነብ መስሎና ሆኖ ተቆጠረ።

ስለዚህም ሲመች የሚይዙት ሳይመች ደግሞ የሚተውት መስሎ ታያቸው። እንዲያም አደረጉ። እስካሁን በታሪክ እንዳየነውና እንዳጠናነው አንሾምም ብቁ አይደለንም ብለው ከሢመተ ጵጵስናው ሸሽተው የቀሩ አባቶች ብዙ ናቸው። ከዚያም ከተሾሙም ወዲያ ሁኔታው አስቸጋሪ ሆኖ ሲያገኙት ወደ ገዳሞቻቸው ትተውት የሄዱና የገቡ አባቶችም ነበሩ አሉም። ከዚያ ውጭ ግን እንዲህ እንዳሁኑ እንደ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በማያሻማ ቋንቋ በግልጽ በገዛ ፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን አስረክበው የጡረታ መብታቸው ተከብሮላቸው መኪና እስከ ሾፌሩ ተመድቦላቸው ተቀምጠው መልቀቃቸውን በራዲዮና በቴሌቪዥን ተናግሮ እሳቸው ሥልጣኑን ካስረከቡ ካንድ ዓመት በኋላ ተተኪ የሚሆን አባት በምርጫ ከተሾመ በኋላ ከዚያም አንድ ዓመት በድምሩ ሁለት ዓመት ቆይታ በኋላ ከነበሩበት በዓት ጥለው ጣጥለው ወደ ኬንያ ስደት ሄዱ። በኬንያ ከተወሰኑ ዓመታት ቆይታ በኋላ ወደ አሜሪካ መጡ። ከሌሎች አባቶች ጋር በመሆን ከተበረታቱ በኋላ ወደ ሥልጣናቸው ለመመለስ እንኳ ሳይሆን ከዚሁ ካሉበት ሆነው እኔ ነኝ ማለት እንደሚችሉ አበረታቷቸው። ሲኖዶስ አሜሪካ መጣ ገባ ሲሉ ያላንዳች ፍርሃት በድፍረት አወጁ። ኢትዮጵያ የለም የሚል ዜና ተፈጠረ። እነሱን ያጸጸሰ ቅዱስ ሲኖዶስ ኅልውናው መኖሩ ተከዳ። ተኳሚ ሲከዳ ኳሚ እንዴት አይካድም። የተፈጥሮ ሞት የሌለበት የመንፈስ ቅዱስ የአንድነት ጉባዔ ኅልውና ተደመሰሰ። መንበሩን ለቆ አሜሪካ ገባ ብለው ሠበኩ። እንዴት ተብሎ አይጠየቅ መልሱ ብዙ ነው። ቢጠፋ

ቢጠፋ በታምር የሚል መልስ ማንም የማያንከባልለውና የማይገፈትረው ተራራ አለና ነው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክነታቸውን ቃለ ምዕዳን በሚያሰሙባቸው በአካባቢው ራዲዮ ጣቢያዎች ማዕርጋቸውን ያነቡ ጀመር። ለካስ ለሌላው ዝግጅት ለማለማመድ ኖሯል። ለብዙኃኑ ግን የተረዳው ከሥልጣንም ቢለቁ ስሙን የሚጠሩበት እንጂ የሚሠሩበት አልመሰለንም ነበር። ቀስ በቀስ ሕጋዊው ፓትርያርክ የሚለው ቅጽል ተጨመረ። በአሜሪካ ሕግ ወይንስ በኢትዮጵያው ሕግ? አልተለየም። ሁሉም ነገር በምሥጢር ተያዘ። ነገር ግን ውስጥ ውስጡን እንዲያሰሙና ማንነታቸውን እንዲገልጹ ይደረግ ጀመር። በዚያው ቀጥሎ እነሆ አሁን ከደረሰበት ደረጃ ደረሰ። አሁን ይፋ ወጣ ኤጲስ ቆጶሳት ተሾሙ። እሳቸው ግን ተወገዙ። የመጀመሪያው በፈቃድ ሁለተኛው ግን በግድ ሆነ።

ቀደም ያለሽረት በምሕረት የተያዘው ጉዳይ ከመሥመር ወጣ። አሁን የመጣው ይምጣ ሆነ። ይህን ችግር ተዉ ይብቃ የሚለው ማነው? ቅልም ተሠብረ አሞራም በረረ ሆናልና! ቤተ ክርስቲያናችን እንኳን በሕይወት ሳሉት ይቅርና ለሙታን እንኳ የምትጸልይ ከፈጣሪ የምታስታርቅ ናትና ከባድ አይደለም አይሆንምም። እንደገና ሊስተካከል ይችላል። ይቅር መበባልም አይጸንም። አሁንም በጎ ፈቃዱ ካለ ነው። በጎ ፈቃዱ ከሌለ ደግሞ ከጲላጦስ ዓቢይ ነገር ተምረናል። እሱም ዕጅን ታጥቦ ከበደላችሁ ንጹሕ ነን ማለት ነው። እነሱ እሺ ባይሉ ተተኪዎቹ እሺ ይላሉ። ካሉን የመጽናኛ ተስፋዎች ውስጥ ይህ አንዱ ነው። ይሁንና የዘወትር ጸሎታችን እግዚኦ ዕቀቦ [ጌታ ሆይ ጠብቀው] ብለን መጸለያችን ይቅርና ሌላ ይሆናል። እሱን ለእግዚአብሔር ነው የምንነግረው። ለሚውም አድራጊውም እሱው ነውና ነው። ይህ አንዱ በጸሎት ፈልገን የምናገኘው ክርስቲያናዊ መፍትሔ ነው። በሰው ሰውኛ ግን የሚቻል ቢሆን ኖሮ እስካሁንም ይሞከር ነበር። አሁንም ከእነሱ የምንወጣ የምንገባ ምዕመናን ታላቅ ድርሻ አለን። ተዉ ይብቃ ወደ በላም ምጡ ብንል ተሰሚነት አለን። ምክንያቱም ካልሰሙ የማርያም መገበሪያው ወይንም ማርያም ባርኪው ፍሬ ግብሩ ይቋረጣልና ነው። ከሆነ የተባበሩት መንግሥታት ዓይነቱ ማዕቀብ ያልሆነ መጣልና በሥራ መዋል አለበት።

ምዕመናን በዚህ ሁኔታ ላይ ቤተ ክርስቲያናችንን እያየንና እየተመለከትን ዝም ብለን ማለፍ የለብንም። ለዚህ ችግር መፍትሔ መሻት አለብን። መቼም የነበረውንና ተከብሮ የኖረውን ቅዱስ ሲኖዶሰ ብዙዎቹ አባቶች የተሠዉበትና ደማቸውን ያፈሰሱበትን በጸሎት በምህላና በጾም በጸሎት ተጠምደው ያቆዩትን ሲኖዶስ



መንበር መነቅነቅ ያውም ለግል ክብርና ዝና ተብሎ ለፖለቲካ ማድመቂያና ማሽብረቂያ ሊገነጠል ቀርቶ ሊነነተል አይገባውም። ቂም በቀልን አጥፍቶ አብሮ መሥራት እንኳን ለአባቶች ይቅርና ለተራ ምዕመን እንኳ ይቻላል። ከዚህ ውጭ ግን እነሱ አንታረቅም ሰላም አንፈጥርም ካሉ እኛም ሰላማችንን መንሳት አለብን። ምርጫችን ቤተ ክርስቲያናችን ወይንስ ሽማግሌ አባቶችን? ይህ አይሆንም። አሊቃ እንዳሉት በቤተ ክርስቲያናችን ምንም ነገር ይሁን ምን ጤናማዋን ዘለዓለማዊቷን ቤተ ክርስቲያናችንን ነገ ከነገ ወዲያ በሚያልፉና በሚጠፉ ሥጋ ለባሽ አባቶች ብለን በምንም ታምር አንለውጣትም። አንድነቷ ይጠበቅ። ቅርንጫፍም ሆነ ሥር ወይንም ሕጋዊም ሆነ ኃያለ ኃያላን ሲኖዶስ አሜሪካ በቀል አንቀበልም። እንዲያው ከአሜሪካ የሚሠራውን ሁሉ ተቀባይነታችን ቢታወቅም ቅሉ ብለን ብለን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የሚከፍልና የሚሸረሽርን ምንም ይሁን ምን አንቀበልም። ምዕመናን ጥግ እንያዝ።

ተዉ አይሆንም እንበላቸው። እምቢ ካሉ አንኳን ሙዳየ ምጽዋታችንን መንሳት ይቅርና ዕጅና እግራችንን እንኳ መንሳት ሃይማኖታዊ ግዴታ አለብን። አሜሪካ ለበቀለ ሲኖዶስ ሕጋዊም ይበሉት ባለ «ግሪን ካርድ» በምንም ዓይነት የማሳደጊያ ቀለብ አንሰፍርም። ክብር ወግ ማዕርግ ከፈለገ ወደ ቤቱ ሥልጣነ ክህነቱን ወደ ሠጠ ወደ አጸደሰ ሲኖዶስ ይመልሱት። እነሱም ወደ ሕጋዊው የጋራ ጉባዔያቸው ወደ ቅዱስ ሲኖዶሱ ተመልሰው ይቅር ይበባሉ እንመማር ተበዳድለናል ይበባሉ። ያለው ዕድል ይህ ብቻ ነው። ያለበለዚያ በሕይወት እያለን ሳንሞት ቤተ ክርስቲያናችንን ለጥቂቶቻችሁ ሹመትና ክብር ስንል ከፍለን አንሞትም። ጥላችሁት የመጣችሁትን ክብር ትታችሁትም የምትሄዱትን ምሥጢር በሰው አገር እንደ ካባ ደርቦ እንደ ቀሚስ አጥልቆ መልበስ መልካም አይደለም አያደምቅም አያሳምርም። ይልቁንስ ያንገት መነቅነቂያ የጠላት መሳቂያና መሳለቂያ መሆን ነው።

አሜሪካ የሚሠራ ሁሉ ዕቃ ኢትዮጵያ ልትሸምት አቅምም ጉልበትም የላትም። እንዲያው ሌላው ያሳነሰን ደግሞ ጵጵስና ከአሜሪካ መጥታችሁ ታመርቱልን? ምነው ካቶሊኮችን አትመለከቱም? ምነው ግሪኮችን አትመለከቱም? ምነው እናንተን የሥልጣን ካባ ለማሰፋት ለመደረብ አስፈለጋችሁ? ይህ በሰው አገር ያውም በእንግድነት ያውም በስደት ይህን ያህል ዓቢይ ሥልጣነ ክህነት የምታውሉበትና የምታሳድሩበት ለመሆኑ ቦታስ አላችሁን? የትም ልታውሉት ልታሳድሩት? እሱስ ከፍተኛ ታላቅ ቦታ አለው።

ምን ይምጣ? ስለ ምልጃ ስለ ይቅርታ ስለ ንስሐ ስለ ሰላም ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ህልውና ማሰብ ከእናንተ ከብፁዓን አባቶች ወዲያ ለመሆኑ የሚቀርብ አለን? የለም አይገኝም። ነገር ግን ማሳሰብ መወትወት የግድ ነው። እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ አሥራ ሁለት ጊዜና ከማሁ በእንተ ማርያም አሥራ ሁለት ጊዜ የተለመደው ጸሎት የጸሎት አቀራረብ ነው። ይህም ቢሆን ኪራይላይሶን ዓርባ ዘጠኝ ጊዜና አሥራ ሁለት ጊዜ አቡነ ዘበሰማያትን መጸለዩን እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው። ስለዚህ ወደ አባቶቻችን የመቅረቡን ፀጋ ያገኛችሁ ሁሉ አባካችሁ ሳትሰለቹ ጧትና ማታ ቀጥሉ አትሰልቹብን። ያሰብነውን ሰላም እንድናገኝ በተስፋና በእምነት በርቱ። ይሆናል ይሳካል። ከዚህ ከገጠመን ፈተናና መከራ ቤተ ክርስቲያናችንን እናድናት።

አሁን አባቶችም እኛም ያለነው በሰው አገር ነው። ምንም ሕጋዊ መታወቂያ ደብተር ሠጥተውን ብንኖርም የሠጠ ዕጃቸው መልሶ የማይወስድበት ጉልበት ያንሰዋል አይባልም። አንድ ቀን እነሱንም ጠብ ጠብ ቢላቸው እንዲያው የኢሚግሬሽን ጽ/ቤት ቢቆጣ ውጡ ቢል እንደ ውሀ ሙላት ጠራርጎ ቢያስወጣን ወዴት ነው እግራችንን የምንሠነዝረው? ያን ጊዜ ነው ታምር ተፈፀመ የሚሆነው። ለምን ተናገር ተናገር እንዳለኝ ባላውቅም ፍርሃት አለኝ። የአሜሪካና የኢትዮጵያ ዝምድና ከጓደኝነት ዘለል ብሏል። አባቶች ተጠንቀቁ። የምትሠሩትን እወቁ። ወደ ሰላሟ በር አባካችሁ ዝለቁ።

ብፁዓን አባቶቻችን በዚህ በአሜሪካ ቆይታችሁ ከቦታ ቦታ በመሽጋገር ካንዱ ደብር ወደሌላው በዝውውር ከታየና ከተጠና በኋላ በተገኘው ልምድ በተደረገው ስብከትና አመክሮ አሥር ዓመት መቆየት። በዚህ ሁኔታ በአሜሪካ መንበር መመሥረት ሆነ። እንደዚሁ የሩሲያዊዋ ቤተ ክርስቲያን እንደ አርዓያም እንደ ምሳሌም ትታይ ነበር። እነሆ ከእናት ቤተ ክርስቲያኗ ጋር እሷም አንድነት ፈጠረች። ታዲያ እኛስ እንደ እነሱ ወደ አንድነቱ አይመጣም? መልካም ምሳሌም ሆኑልን። የቤተ ክርስቲያናችን አንድነት ከምድራዊው ሕይወት የበለጠ ዋጋ የምንሠጠውና የምናከብረው ጉዳይ ነው።

እንደ አመክሯችን የተበደለ ሰበደለ ጸልዮ በዚያም ላይ ይቅርታ ጠይቆ ቢያደርገው ያስከብራል ትሑት ያሰኛል። በምዕመናንም ዘንድ እጅግ ያስወድዳል ፈጽሞም ያስከብራል። ያለ ሰላሙ ያለ ፍቅሩ ሌላ ምንም ነገር የሚረባም የሚጠቅምም የለም።



የእናንተ የአባቶቻችን አንድነት ማጣት ለኛም ልቅሷችን ቅጥ ያጣ ይሆናል። እንደተባለውና እንደተነገረውም ሁላችንም እንደምናውቀው የልቅሷችን ዝዬ የሚሆነውና የሚባለው «የሞተውም ባልሽ፥ ገዳዩ ወንድምሽ፤ ኃዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ።» ይሆንብናልና ተማለዱን አንድ ሁኑልን። እናንተኮ በስምና በአካል እንጂ ልዩነታችሁ በሥልጣን በጉባዔ በአምልኮ በመንበር አንድ ናችሁ። ያውም የተዋሕዶ የአንድ ባሕርይ አባቶች ናችሁና ይኸው ይጽናልን ይፈጸምልን። የምዕመናን ልመና ምልጃ ልቅሶና ሥዕለት ማቅረብ ያለመሰልቸት ማድረግ ይገባናል።

ቀደም ሲል ለልዩነቱ አርዓያ ሆና የቆየችው የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አሁን ለአንድነቱ ለሰላሙና ለፍቅሩ አርዓያነቷ ከተራራ ላይ ያስቀመጧት መብራት ሆናለች። ይህች የሩሲያዊዋ ቤተ ክርስቲያን ከእናት ቤተ ክርስቲያኗ ተለይታ አሜሪካ መንበር መሥርታ ቆይታ ነበር። አሁን እነሱም ያን ልዩነታቸውን አፍርሰው ግንቦት አሥራ ሰባት ቀን ሁለት ሺህ ሰባት ዓመተ ምሕረት [5/17/2007] እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር አንድ ሆኑ። ይህን የአንድነት በዓል የሩሲያው ፕሬዚዳንት ፑንት በተገኙበት መስኮብ ከሚገኘው በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ድምቀት ተከበረ። በበዓሉም ላይ በፓትርያርክ አሌክስ ሁለተኛ የሩሲያ ፓትርያርክና በአሜሪካ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የበላይ ኃላፊ የሆኑት ላቭር የአንድነቱ ቃል ኪዳን ፀና። እንኳን ደስ ያላችሁ። ይህን ዜና የሰማሁት ይችን የአቤቱታ ደብዳቤ እየሞነጫጨርሁ ባለሁበት ጊዜ ስለሆነ እጅግ ደስ የሚል የምሥራች ድምፅ ተሰማኝ። ፊቴ በኃዘን ጠውልጎ የነበረው ወዙ ጨንቧ አለ። የኛም አባቶች አሜሪካ ሲቀር መንበሩ የሚቀር ቢሆንም ቅሉ በሕይወታቸው እያሉ ታሪካቸውን ቢአድሱ እንዴት መታደል ነበር? ብዬ ተመኘሁ። አቤት ልልበት የነበረውን የእንጉርጉሮ ቅላጼ ሁሉ በል ተወው ሲሆን ወደ አንድነት ነገ ከነገ ወዲያ ይመለሱ ይሆናል። ካልሆነ ደግሞ ከእነሱ በኋላ በሁሉም ዘንድ ወደ አንድነቱ ይመጣል የሚል የተስፋ ድምፅ በጆሮዬ ሰማሁ። እኔም ያስ ባይሆን እነሱ ለዘለዓለም አይኖሩ ብዬም ተጽናናሁ። ነገ ከነገ ወዲያ ልዩነቱ ይመዘበራል ይቀራል ኃዘንህንና ልቅሶህን አቁም የሚል መንፈስ መጣልኝ አበረታታኝ አጽናናኝ። ይህን የሩሲያን ቤተ ክርስቲያን ተክፍሎ መኖር ሳስብ ለኛም ሰዎች አርዓያነቱን አልወደድሁትም ነበር። ስለሆነም እንዲያው ይኸው የሩሲያም ቤተ ክርስቲያን ተከፍላ ትኖራለች ምን ሆነች? ተከታይ አስካለ ድረስ ይባላል ብዬ ሠግቼ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር ታምር ቀደመና ቦታ ያዘ። እ ኛም እንደዚሁ የቀረው ይቅር ለቤተ ክርስቲያናችን ክብር ብቻ ሳይሆን

ለሰሚና ለተመልካችም ግራ የሚያጋባ ነው። መጽሐፉ ሌላ በተግባር የምናየው ሌላ መንገዱ እንኳ አንዱ ባንዱ ላይ አያቋርጥም። አንዱ በላይ አንዱ በታች ማዶ ለማዶ የሚተላለፍ እኛስ ምን እንበል? ይህ ቅዱስ ጳውሎስ ለራሱ ብቻ ነበርን የተናገረው? የኛዎችን ብፁዓን አባቶችን አያጋራምን? ለካህናቱ አያካፍልምን? እሱስ ታሥሮ ቴንገላቷል። ከመካከለኛው ምሥራቅ ሮም ድረስ በእሥረኛነት ተጉዞ ሮም ላይ ለቤተ ክርስቲያኑ በገባው ቃል መሠረት አንገቱን በሠይፍ ተቀልቶ እንደ በግ ታርዶ ሩጫውን ፈጽሟል። የገባውን ቃል ኪዳን በትክክል ፈጽሟል። ሞትን ለፈሩስ ቢኖሩሳ ምን ይላቸው ነበር? ሌላ ያለውን ለእንዲህ ላሉት ሠባክያነ ወንጌል ያለውን እንናገር? ምች ማስመታት ይሆናል እንዲያውም ምች አደሩ በዝቷል የሚያነብ ያንብበው።

ብፁዓን አባቶች ካህናት ምዕመናን ሁላችንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች ተከታዮች ቤተ ክርስቲያን ተሳላሚዎች በሙሉ ስለዚህ ጥንታዊት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን እንጠንቀቅ አባቶቻችን እንዳስረከቡን ጠብቀንና ተንከባክበን ማስተላለፍ ሃይማኖታዊ ብሔራዊ ሰብአዊ ግዴታዎች አሉብን። በእግዚአብሔር ዘንድ አለቃና ጭፍራ የለም። ሁላችንም እኩል ነን። ይህም ሲባል መከባበር ይረሳ አይደለም። የበለጠ መሆን ያለበት መፈፀም ያለበት እንጂ! ይሁንና አሁን የት ነው ያለነው? በዚች ቤተ ክርስቲያን ላይ የምንሠራው የምንፈጽመው በእውነት ስለ እውነት የሚጠበቅብንን ነው? ወይንስ ይህን ዓለም ስንኖር ዋኝተን የምንወጣበትን አቋራጭ ብቻ ወንዝ ተሺግሯል ለመባል ነውን? እናስተውል እንመልከት እኛ ዘለዓለማዊ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደለም። በትንሽ ነገር መተንፈስ የምቷቋርጥ እጅግ በጣም በጥቂት ነገር እንዳልነበረች የምትሆን ሥጋ ላይ ነው ውለን የምናድረው። በጥሞና ካሰብንበት ለምን እጨነቃለሁ? ለምንስ እንገላታለሁ ላይሆን ለምን ክፉ ሥራ በመሥራት እታወቃለሁ ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይገባናል። አቤቱታው ለበጎ ነገር አርዓያ እንሁን ነው።

ስለዚህ ምን እናድርግ? እነሆ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይለናል። «ወአንስ እብለክሙ አፍቅሩ ጸላአተክሙ ባርክዎሙ ለእለ ይሰዱድክሙ ሠናየ ግበሩ ለእለ ይጸልኡክሙ ወጸልዩ በእንተ እለ ይትዔገሉክሙ» [እኔ ግን እላችኋለሁ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ። ማቴ. 5:44] ከዚህ ወዲያ ምንም ዓይነት ቃል አያስፈልገንም ይህ እጅግ በጣም በቂ ነው። ስለሆነም



የጥላቻ ኮረጆ ይተርተር። ሰላምና ፍቅር ይዳብር። የቤተ ክርስቲያናችንን ህልውና እናስከብር። ጥላችንን በንስሐ እንጠብ። በአንድነት እንኑር። የአባትና የልጅነታን ትስስር ይጥበቅ። ልጅ ሲያጠፋ አባት ይምከር። አባትም ሲሰሳት ልጅም ይንገር።

ይህን ቃል መመሪያችን ካደረግን የምንጠላቸውን ከወደድን ምን ችግር አለብን? ይህ ደግሞ አሜሪካ አውሮጳ አውስትራልያ አፍሪቃ ኤሲያ ኢትዮጵያ መበባል ሳይኖር እንዲት ሃይማኖት እንዲት አገር ያንድ ሰው ዘር ነንና ፍቅራችን ባንድነት ይማገር። ለየግል ለየብቻ የምንሠራው መነጣጠሉ ለኛ ሳይሆን የሚያገለግለው ቤተ ክርስቲያናችንን ለሚያጠፉትና ለሚመዘብሯት ብቻ ነው። አሳዳጅም ተሰዳጅም አይኑር አንድ ቃል አንድ ጉባዔ አንድ ማኅበር በዚህ ጉዞ እንቀጥል። ይህን ብናደርግ የዘራነው ይበቅላል አድጎና አፍርቶም ይበላል። ሁሉን ለማድረግ የማይሳነው ሕያው እግዚአብሔር በሰላምና በፍቅሩ ይጎብኘን። ጥልንና ክርክርን ከመሃላችን ያጥፋልን። መንፈስ ቅዱስን ያቅርብልን ሠይጣናትን ያርቅልን። በመጨረሻም ብፁዓን አባቶቼ ክቡራን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት ምዕመናን በጠቅላላው ኢትዮጵያውያን በሙሉ ለአገርና ለሃይማኖቱ መቆም መጠበቅ ውሳጣዊ ፍላጎት እንጂ አድርግ ሥራ ተብሎ የማያዝዙት ጉዳይ ነው። ማንም ከማንም አያንስም አይበልጥም ሁሉም ለአገሩና ለቤተ ክርስቲያኑ ያስባል ስትነቀፍ ይከፋል ስትወደስ ይደሰታል። ይህን መሠረት በማድረግ አባቶቼን እናቶቼን ወንድሞቼንና እኅቶቼን በአጻጻፌ ባነጋገሬ ያስከፋሁት ቢኖር ቂም በቀል አትያዙብኝ። ይቅር በሉኝ። ዓላማዬ ለአገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን ቀናዒ በመሆን እንጂ! በጥላቻ ሰው ለመጉዳት ብዬ ያደረግሁት ያለመሆኑን በድጋሚ በእግዚአብሔር ስም አረጋግጥላችኋለሁ። ምን አገባህ ምን ዶለህ? የሚሉ ቢኖሩ የተሠጠችኝን መክሊት ወስጄ ብቀብራት መልካም አይሆንልኝም ብዬ ነው። ከዚህ ውጭ የሚጨመርም የሚቀነስም ምክንያት የለኝም። አረረም መረረም እነሆ! ማኅበሬን ተወጥቻለሁ።

የሰማይና የምድር ፈጣሪ አምላኬ ሆይ! ኃይሉን ድፍረቱን እውቀቱንና ጥበቡን ሠጥተህ ይህን እንድናገርና እንድመሰክር ስለ አደረግህ ምስጋና ለአንተ ይሁን። «አነ ኃጥእ ወአባሲ» እኔ ኃጢዓተኛውና በደለኛው አገልጋይህ ለይኩን ብርሃኑ።

ተፈፀመ።

ኢየሱስ] ፣ *ገድል ወይስ ገደል?* ፤ አዲስ አበባ፣ አፍሪካ ማ/ቤት 1995

ጌታቸው ኃይሌ ፣ *ደቂቀ እስጢፋኖስ በሕግ አምላክ* ፣ ኮሌጅቪል፣ ሚኒሶታ፣ 1996

ግርማ ዘውዴ ፣ *ኢትዮጵስ* ፤ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማ/ቤት 1998

ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት 1992

Ben-Jochannan, Y.A.A. *Africa: Mother of Western Civilization,* Baltimore: Black Classic Press, 1998

Breasted Henry James: *The Dawn of Conscience,* New York, 1933

Brooks F. Miguel, Ed. *The Glory of kings (KIBRE NEGEST).* Laurvencevill: The Red Sea Press, 2002

Felder, Cain Hope. *Troubling Biblical Waters.* Maryknoll, New York: Orbis Boodl, 1989

Hagos Alemayehu: *Live Free! Exposing the Satanic Life & Lies of Western History!,* Gaitsburg: 2005

Hancock Graham, *The Sign and the Seal,* New York: *Crown Publishers Inc.,* 1992

Ivan Van Sertima Ed. *Black in Science Ancient and Modern.* New Brunswick: Transaction Publishers, Inc., 1992

Leykun E. Berhanu: *Contemporary Challenges in the Ministry of the Ethiopian Orthodox Church,* Howard University, Washington, DC: 2005

Means M. Sterling. *Ethiopia and The Missing Link In African History.* Harrisburg: The Atlantis Publishing Co., 1945

Prochazka Roman Baron. *Abssinia: The Powder Barrel.* London: British International News Agency, 1006

Tadesse Tamirat *Church and State in Ethiopia.* London: Oxford University Press, 1972

Teshale Tibebu. *The Making of Modern Ethiopia. 1896-1974,* Lawrenceville: Red Sea Printing Press, 1995

Williams Chancellor. *The Destruction of Black Civilization: Great Issues of A Race From 4500 BC. To 2000 AD.* Chicago: Third World Press, 1987